# አጋንንት፡ በሐይማኖታዊው አድማስ

ዛሬ በክርስቲያናዊ ወንድማማችነት፡ እና በክርስቶስ ፍቅር ሞቅ ያለ ሰላምታ እያቀረብኩላችሁ ይህንን ቀላል መዝሙር የሚያውቁት ሰንቶች እንደሆኑ አሰባለሁ፡ ይህንን ቀላል፡ “እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል” የሚለውን መዝሙር ሰንቶች ያውቁታል? ታውቁታላችሁ? መልካም፡ እስቲ ዘምረን እንሞክረው። ታውቂዋለሽ፡ እኅቴ? ታውቅያለሽ? አይደል፡

እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል፡
እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል፣
በፀሐይ ብርሃንም ሆነ በጥላ፡
እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል።

ኦህ፡ ያ ጥሩ ነው። በድጋመ እንሞክረው።

እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል፡
እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል፣
በፀሐይ ብርሃንም ሆነ በጥላ፡
እሱ ሰለ እናንተ ያሰባል።

[በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

2 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ ሰለ እኛ ሰለምታሰብ እና ለእኛ ያለህን ፍቅር ሰላሳየህ እናመሰግንሃለን፡ ከዚህም የተነሣ የተወደደውን ልጅህን፡ ንጹሕ የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ፡ የ... የኃጢአተኞችን ቦታ እንዲወሰድ ላክኸው። ጌታ ሆይ፡ እኛን ለመንከባከብና፡ ይህን ለማድረግ ሰላሰብከን እንዴት እናመሰግንሃለን! ጌታ ሆይ፡ በጣም እናመሰግንሃለን። ዛሬ ከሰዓት በኋላ እዚህ መሰብሰባችን ደስ እያለን፡ በሰማያት ጥላ ሥር ተሰብሰበን፡ በዚህ አገልግሎት ላይ በረከትህን እንጠይቃለን። ጌታ ሆይ፡ እዚህ ያሉት ወንዶች፡ ሴቶች፡ ወንድ ወይም ሴት ሁሉ፡ አሁን መጽሓፍ ቅዱሰን፡ በጥልቀት እንዲረዱን አድርጋቸው። በሰይጣን ቁጥጥር ሰር ካለው ዓለም ጋር እየተጋፈጥን ነው። አባታችን ሆይ፡ ሰይጣናዊ ኃይል፡ እና በሰዎች ላይ፡ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ሰናጠና፡ ታላቅ እምነት እንዲትሰጠን፡ እና ብዙ ታላላቅ ምልክቶች እና ድንቆች እንዲከናወኑ እንጸልያለን። በክርሰቶስ ሰምና፡ ለእግዚአብሔር ክብር እንጠይቃለን። አሜን።

3 ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ አንድ ጥናት አለን፡ በፍጥነት ወደዛ ውስጥ እንገባለን፡ ወደ አሥራ አምስት ደቂቃዎች ቀደም ብያለው፡ ብዬ እገምታለሁ። አሁንም ሰለ **አጋንንት** እንነጋገራለን።

4 አሁንም ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ ከጓደኞቼ መካከል፡ ከወንድም ቢለር፡ አንድ መልዕክት ደርሶኛል። በሐምሌ ወር አጋማሽ ላይ፡ በአፍሪካ እጀምራለሁ። ሰለዚህ ተወሰኗል፡ አሁን ተሰተካክሏል። በዚሁ ወቅት ወንድም ባክስተር አይሄድም፡ ወደ አፍሪካ ብቻዬን መሄድ ይጠበቅብኛል። ሰለዚህ ከእነ... እንግዲህ... አሁን ጌታ እንዲረዳኝ፡ ሰለ እኔ ጸልዩ፡ ምክንያቱም አሁን ጸሎት

በጣም ያስፈልገኛል፡ በዚያ ቦታ... በዚያ ስብሰባ ላይ ቢያንስ ሁለት መቶ ሺህ ሰዎችን እጠብቃለሁ።

5 እዚህ ላይ በጽሑፍ የተቀመጠ ያየሁት ራእይ አለ። እናንተም ከዚህ እንድትማሩ እፈልጋለሁ። ይህ የሆነው በታህሳስ ወር ነበር። አንድ ቀን ጠዋት በክፍል ውስጥ ነበርኩ እና የጌታ መልአክ መጣ። እ... እያችሁ፡ በዚያም ሆኜ፡ እግዚአብሔርን አልታዘዝኩም፡ ስለዚህም አሜባ ታመምኩ። አ—አሜባ ምን እንደሆነ የሚያውቅ ሰው አለ፡ ሊገድላችሁ የ... የሚችል ታህዋስ ነው። ይህም የሆነው እግዚአብሔርም እንዳላደርግ የከለከለኝን ነገር ስላደረግሁ ነው። ታሪኩን ሰንቶች ሰምታችኋል? አንዳንዶቻችሁ እዚህ እንዳላችሁ እገምታለሁ። በዚህ ተብርናክል ያሉ ሰዎች የሆነውን ታሪክ እንደሰሙ አውቃለሁ። እግዚአብሔር ወደ አንድ ቦታ እንድሄድ፡ **ከዚህ** ቦታ እንድርቅ፡ ወደ ሌላም ቦታ እንድመለስ ነገረኝ። እኔም ሰባኪዎቹ በንግግር እንዲያታልሉኝ እራሴን አሳልፌ ሰጠሁ። እንግዲህ፡ ሰባኪዎቹ ጥሩ ሰዎች ናቸው፡ ወንድሞቼ ናቸው፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን ሰሙት። በትክክል። እያችሁ? ተልዕኮአችሁ አንድ ናት።

6 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ ወቅት ሁለት ነቢያት እንደነበሩ ሰንቶቻችን እናስታውሳለን? ከእነሱም አንዱን፡ ጌታ ተናገረው፡ እንዲህ አለው፡ "**እንዲህ** ወደተባለ ቦታ ሂድ። በዚያም... .እንዳትመለስ—በሌላም መንገድ ትመለሳለህ፡" ወዘተ ነገረው። "በዚያም እ—እንዳትበላ ወይም እንዳትጠጣ፡" አለው።

7 ከዚያም ሌላ ነቢይ የሆነ ሰው ተገናኘውና፡ "ጌታ አንተን ከተገናኘ በኋላ እኔንም ተገናኘኝ፡" አለው። "ወደ ቤቴ ግባ፡" አለው። እና ነቢዩ ሌላ ሰው የተናገረውን ሰምቶ፡ ሕይወቱን አጣ። እያችሁ፡ ሌሎች የሚሉትን ሳታዳምጡ እግዚአብሔር የሚጠይቃችሁን ነገር አድርጉ።

8 እና እንዲህ ሆነ... በዚያ ራእይ፡ እነሆ... እነቃኝ፡ መስከረም አሥራ ሦስት-... ወይም ታህሳስ ላይ። እ—እና አልጋዬ አጠገብ ቁጭ ብዬ፡ የወደፊት ሕይወቴ ምን ሊሆን እንደሚችል እያሰብኩ ነበር። እኔ... ወደዚህ ስመለስ፡ የተላላፊ በሽታ ማቆያ ውስጥ ሊያስገቡኝ ተዘጋጅተው ነበር፡ አሜባ ሊገድለኝ ተቃርቦ ነበርና። እግሬ ምድሪቷን እንደረገጠ ወዲያው መርመሩኝ። በእግዚአብሔርም ጸጋ፡ ወደ ቤት እንድሄድ ፈቀዱልኝ፡ ምክንያቱም ህመሙ በጣም ግራ የሚያጋባ ነበር። እኔም ጸለይኩበትና፡ ወደ አገልጋዮቹ ሄጄ፡ "ጌታ በዚያ መንገድ አትሂድ ብሎኛል፡" አልኳቸው።

"ተው እንጂ፡ እግዚአብሔር ከአንተ ውጪ ለሌላ ሰውም'ኮ ይናገራል፡" አሉኝ።

9 እኔም "ቆሬም በአንድ ወቅት እንዲህ ዓይነቱ ሃሳብ አስቧል፡" አልኳቸው። እናም ሄጄ፡ የተወሰኑ ቅጠሎችን አመጣሁና በእግሮቻቸው ላይ አኖርኩት፡ እንዲህም አልኳቸው፡ "በጌታ ስም፡ አስታውሱ፡ ወደዚያ ጉዞ ካደረግን፡ ውድቀት ይሆናል፡ ሁላችንም ዋጋ እንከፍላለን።" እናም በትክክልም ከፈልን! ኦህ፡ ማይ! ሁላችንም ሞትን ተመኘን። ስለዚህ ወደ ኋላ...

10 በእነዚያ የውጭ አገሮች ውስጥ ብዙ የሚገጥሟዋችሁ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ያህል፡ ትንሽ ቁንጫ ብትነክሳችሁ፡ ትኩሳት ያስከትልባችኋል። እና

ትንሿ ነገር፡ ስትነክሳችሁ፡ የማቃጠል ስሜት ሲሰማችሁ፡ ማከክ አትችሉም። ይኸውላችሁ፡ ጥቁር ነገር ከሆነ፡ ሰባችሁ ለማውጣት እንዳትሞክሩ። ትንሽ ጭንቅላት አለው፡ ወደ ቆዳው ውስጥ ዘልቆ ይገባል፡ **እንደዚህ** ይዞርና፡ እራሱን ይቆልፋል። ጎትታችሁ ብታወጡት፡ ጭንቅላቱን እዛው ታስቀራላችሁ። በውስጡ ቫይረስ አለ፡ ፓራላይዝ ያደርጋችኋል። ስለዚህ... አትከኩት፡ ወይም አትጎትቱት፣ ትንሽ ቅባት ብቻ ተጠቀሙ። የሚተነፍሰው በጀርባው በኩል ነው። በላዩ ላይ ቅባት አርጉበትና፡ በራሱ ይወጣል።

11 ሌላም ትንሽ ቢምቢ አለ። ድምጽ አልባ ነው። በቀጥታ በአየር ይመጣል፡ ከዚያም [ወንድም ብራንሃም እጁን መታ—አርታዒ።] ይነካችኋል፡ በቃ፡ ከዛ ወባ ይይዛችኋል።

12 ሌላ—ደግሞ ማምባ የሚሉት እባብ አለ። ቢነድፏችሁ፡ ከተነደፋችሁ በኋላ ሁለት ደቂቃ ብቻ በህይወት ትቆያላችሁ።

13 ሌላም ቢጫ ኮብራ አለ። ከነደፋችሁ በኋላ ለአስራ አምስት ደቅቃ ያህል ትኖራላችሁ። እንደውም አንደኛው እጁን ዘርግቶ ራሱ መንካት የሚቻልበት ያህል ቀርቦ፡ ወደ ልጄ እጅግ ተጠጋው። እንዲህ ከመተኮሳችን በፊት፡ እሱን ለማጥቃት፡ ቀድሞ፡ ተነሳ።

14 ደግሞም ጥቁር ኮብራ አለ። ኦህ፡ የሌለ ነገር የለም! ከዚያም የዱር እንስሳት አደጋዎች፡ እርግጥ ነው፡ አንበሶች፡ ነብር፡ ወይም አነር፡ በጫካ ውስጥ፡ ከሁሉም ነገር ጋር መዋጋት ነው። ከዚያም በሽታዎች፡ ሁሉም ዓይነት በሽታዎች አሉ።

15 እናንተም ስትሄዱ ይህን ሁሉ ትጋፈጣላችሁ። ከዚህም ባሻገር፡ በየአቅጣጫው የሚፈታተኗችሁ ጠንቋዮች፡ አያችሁ፡ ያላቸው ዐጉል እምነቶች እና ነገሮች ሁሉ አሉ። ነገር ግን፡ ጌታችን ራሱ፡ ከጥግ እስከ ጥግ፡ እንዲህ ሲያናውጣቸው ማየት፡ እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው፡ ከዚያም መንገዳችንን እንቀጥላለን።

በዚያም ቀን አስታውሳለሁ፡ በዚያ ቆሜአለሁ፡ እንዴት እንደሆነ፡ ምን እንደሆነ፡ በሌላ ሰብሰባ ላይ ሌላ ጊዜ እነግራችኋለው፡ ምክንያቱም ዛሬ ከሰዓት በኋላ በርዕሴ ላይ፡ ስለ **አጋንንት** መናገር ስለምፈልግ ነው።

16 አሁን ግን፡ እዚያው ቁጭ ብዬ፡ እንዲህ እያሰብኩ ነበር፡ መጨረሻው ምን ይሆን? ከባሕርም ማዶ ስንመለስ፡ እዚያ በነበርንበት ጊዜ ወደ መቶ ሺህ የሚጠጉ ጌታን ለመከተል የወሰኑ እንደነበሩ አውቃለሁ። ሽማግሌው ወንድም ቦስዎርዝም ወደ እኔ መጣ። እንዲህ፡ አልኩት፡ "እሺ፡ ወንድም ቦስዎርዝ? "

17 እንዲህ አለኝ፡ "በጣም እኮራብሃለሁ፡ ወንድም ብራንሃም!" አለኝ፡ "አንተ'ኮ ገና—ገና በሕይወት ጅማሬ ላይ ነህ፡" አለኝ።

18 እኔም "እኔ ግን፡ ሁሉ አልቋል ብዬ አሰባለሁ፡" አልኩት። "አርባ ዓመቴን አልፌያለሁ። መልካሙን ገድል ተጋድዬ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ብዬ አሰባለው፡" አልኩት።

19 እርሱም፡ "'አርባ ዓመቴን አልፌያለው'? " "እኔ ጌታን ከመቀበሌ በፊት ዕድሜዬ የአንተን ያህል ነበርኩ፡" አለኝ። "አሁንም ጥሩ እየሰራሁ ነው፡" አለኝ። ወደ ሰማንያው ተቃርቦ ነበር። እና...

“ደህና፡ ምናልባት ትክክል ሊሆን ይችላል፡” ብዬ አሰብኩ።

20 ስለዚህ እንዲህ አለኝ፡ “አይ፡ አንተ አሁን ኒው ብራንድ ብራንሃም ነህ። ስብሰባዎችህን እና ሁሉንም ነገር፡ እንዴት በተሻለ ሁኔታ መቈጣጠር እንደምትችል ብቻ ተረዳ።” እንዲህ አለኝ፡ “ለስድስት ወይም ለስምንት ሳምንታት መቆየት በምትችልበት ቦታ፡ በማቀናጀትና ማስታወቅያን በመስራት፡ ትክክለኛውን ስብሰባ በማዘጋጀት፡ አሜሪካን በትክክለኛው መንገድ ብታገኛት፡” “አንድ ነገር ታደርጋለህ፡ ነገር ግን፡ ለአምላካችን ነው፡” አለኝ። ስለዚህ እንዲህ እያልን፡ ወደፊት ቀጠልን፡ ስለዚህ በጣም—በጣም ጥሩ ነበር።

21 ከዚያም ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ በአሜሪካ ሳለሁ፡ አንድ ራእይ አየሁ፡ ራእዩ ወደ እኔ መጣና፡ ወደ አፍሪካ መለሰኝ፡ እና በደርባን ፊት ለፊት የተቀመጠውን፡ ያንኑ ስብሰባ አሳየኝ። የመጀመሪያውም ስብሰባ ጥፋና ታሪክ ሆነ፡ ወደ ምዕራብ ሄድኩ። ሁለተኛው ስብሰባ ተነሣ፡ ሲነሳም፡ ከመጀመሪያው ስብሰባ የበለጠ ነበር። እ... እኔም የጩኸት ድምጽ ሰማሁ፡ መልአክም ከሰማይ ወጣ፣ ታላቅ ብርሃንም አበራ።

22 በዚህ በአጠገቤ የሚቆመው የእግዚአብሔር መልአክ፡ ቆሞ ነበር-... ሁሌም በቀኜ፡ **በዚህ** በኩል ይቆማል። በዚያም ቆሞ ነበር፡ እነሆ—እርሱም ይዞር ነበር። አንድ ሰውም ከበታችሁ ቆሞ አየሁት። አሁን፡ እ—እሱን ስታዩት... .ራእይ አይደለም። እናንተ እኔን እንደምታዩኝ አይነት ገሃድ ነው። ማለት፡ እኔ ሰራመድ ከእናንተም ጋር ስነጋገር ትሰሙኛላችሁ። እርሱም... እንደ ማንኛውም ነገር፡ እንደ ገሃድ ነው። ራእይ አይደለም፣ ሰውዬው ልክ እንደ እናንተ እንዲሁ በዚያ ቆሟል። ድምጹም እንደ እኔ ወይም እናንተ ዓይነት ተመሳሳይ ድምጽ ነው። ነገር ግን ራዕይ፡ በፊታችሁ እንደ ድንገት ድቅን የሚል እና የምታዩት፡ እንደዛ ነገር ነው። ነገር ግን ይህ ሰው መጣና ቆመ።

23 ስለዚህ ምን ሊሆን... እንደሚችል ነገረኝ። እና ተናገረኝ... መልአኩ ወረደና፡ እንድዞር እና **ወደዚህ** እንድመለከት ነገረኝ። አሁን፡ ወደ ህንድ አካባቢ ይመስላል። ህንድ ውስጥ ነው አላልኩም፡ ግን ወደዚያ ይቀርባል። ሰዎቹ ግን የህንድ ሰዎች ነበሩ።

24 ምክንያቱም፡ አፍሪካውያን ትልቅ፡ ጠንካራ፡ ከባድ ወፍራም-የሆኑ ሰዎች ናቸው። አንዳንዶቹ፡ ሰባት-ጫማ ቁመት ያላቸው ሲሆን፡ ክብደታቸው፡ ኦህ፡ ደግሞ ሁለት መቶ ሰማንያ፡ ሦስት መቶ ፓውንድ ነው። ዙሉዎች፡ እና፡ ሻንጋያን እና ባሱቶ፡ እና፡ ኦህ፡ ብዙ የተለያዩ ጎሳዎች አሉ። በዚያ ቀን እየተናገርኩ በነበረ ቀን፡ አስራ አምስት የተለያዩ ጎሳዎች ተቀምጠው ነበር።

25 እኔ አንድ ቃል እናገራለሁ፡ እንደዚህ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ።” ሁሉም አስተርጓሚዎች ቶርጉመው እስከሚጨርሱ ድረስ ውሃ ለመጠጣት እሄድ ነበር። አንዱ ሲናገር... ሁሉም ይጮኻሉ!

የጴንጤቆስጤ ሰዎች በልሳኖች ሲናገሩ፡ ስሰማ አንድ ሰው በአንድ ዓይነት ድምፅ ሲናገር፡ ሌላኛው ደግሞ በሌላ ዓይነት ድምፅ ሲናገር፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብዬ አስብ ነበር? ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል እንደሆነ አምናለሁ፡ እናም እንዲህ ሲል፡ ትክክል እንደሆነ አውቃለሁ፡ “ትርጉም የሌለው ድምፅ የለም።” በትክክል።

አንዳንዶቹ እንዲህ ይላሉ፡ አንዱ “ብሪር ብሪር ብሪር ብሪር፡” ይላል፡ ትርጉሙም “ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ” ማለት ነው። ሌላኛው ደግሞ “ክሉክ ክሉክ ክሉክ ክሉክ፡” ይላል፡ ይህም በራሱ ቋንቋ “ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡” ማለት ነው። ስለዚህ የድምፅ ዓይነት ምንም ይሁን ምን የሆነ ቦታ ትርጉም አለው። በትክክል። ምንም ዓይነት ድምጽ፡ ለአንድ ሰው አንድ ነገር ማለት ነው። እና ያ በነበረ ጊዜ... ያንን ያሰማሉ።

26 በግራዬ በኩል ደግሞ መልአኩ ሲወርድ አየሁና፡ አንድ-መንጋ የሚመስል ነገር አየሁ፡ ሰዎችም ነበሩ... በላያቸውም፡ **እንዲህ** ያለ፡ እንደ ጨርቅ መሳይ የ—የነበራቸው ይመስሉ ነበር፡ በህጻን ልጅ፡ እንደተጠቀለለ ጨርቅ። እንደዛ ይመስል ነበር። እኔም ማየት የቻልኩትን ያህል ርቀት አየሁ፡ ከብዙ ህዝብ በቀር ሌላ ነገር አይታይም። መልአኩም አንድ ትልቅ የሚያንቀሳቅስ ብርሃን አበራ፡ እና ወደ ፊት እና ወደ ኋላ፡ **እንዲህ** መወዛወዝ ጀመረ። በሕይወቴ ውስጥ ያን ያህል ብዛት ያላቸው ሰዎች አይቼ አላውቅም!

27 ከዚያም ሌላ መልአክ ወደ እኔ ቀረበና፡ “በስብሰባው ላይ ሦስት መቶ ሺህ ሰዎች አሉ፡” አለኝ። እዚህ ጋር ጽሬ ይዤዋለሁ። እና በፊንላንድ ውስጥ ስለተነሳው ትንሽ ልጅ እንደነገርኳችሁ፡ በቍራጭ ወረቀት ላይ ጽፋችሁ ያዙ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወይም በባዶ ወረቀቶች ወይም በሌላ ቦታ ጽፋችሁ ያዙት፡ ማለት ያ ስብሰባ (ስብሰባ ይደረጋልና። ከአንደንድ ዜና አውታሮች ትሰሙታላችሁ።) በስብሰባው ላይ ከሦስት መቶ ሺህ በላይ ሰዎች ይገኛሉ። አሁን፡ ያ ትክክል ካልሆነ ታያላችሁ። ያ ከመጀመሪያው ከነበረው በሦስት እጥፍ ይበልጣል። አያችሁ? ስብሰባው ላይ ሦስት መቶ ሺህ ሰዎች ይገኛሉ። እዚያም ለመድረሴ በጣም ደስ ይለኛል፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡ ምክንያቱም ለጌታችን ነፍሶችን መማረክ እወዳለሁ።

28 እዚያም፡ በአንድ ጊዜ፡ ሠላሳ ሺህ ጥሬ አረማውያን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጡ—አይተናል በአንድ መሠዊያ ጥሪ፡ ሠላሳ ሺህ ጥሬ አረማውያን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መጡ።

29 አሁን በፍጥነት ወደ ርዕሳችን እንሂድ። ትናንት የአጋንንትን ዘዴ ተምረናል። ዛሬ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፡ እያሰብኩ ነበር። መውጣት ምን ያህል ነጻነት እንደሚሰጥ አታውቁም። አሁን፡ እኔ አስተማሪ አይደለሁም። የ—የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ከመሆን በጣም የራቅሁ ነኝ። እኔ የተማርኩት... እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ ነው። ስለዚህ... እና፡ ከትምህርት ገበታ የወጣሁት የዛሬ ሃያ-አምስት ዓመታት በፊት ነው፡ ስለዚህ፡ በጣም ረጅም ጊዜ ነው። ብዙም ትምህርት የለኝም፡ ነገር ግን የማውቀው ነገር ሁሉ የተቀበልኩት በምሪት ነው። ያ ምሪትም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይመሳሰል ከሆነ፡ ስሕተት ነው። አያችሁ? ከመጽሐፍ ቅዱስ መሆን አለበት። ምሪት ምንም ይሁን ምን፡ ከመጽሕፍ ቅዱስ መምጣት አለበት... የእግዚአብሔር መሠረት **ይኸው** ነው። ከዚህ ሌላ መሠረት የለም። ይህም ምንድን ነው፡ የምናገረው ነገር ከዚህ ጋር የሚቃረን ከሆነ፡ ቃሌን ውሸት ታደርጋላችሁ፡ ምክንያቱም ይህ እውነት ነው። አያችሁ? አያችሁ? መልአክ ከዚህ የተለየ ነገር ቢነግራችሁ፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ የብርሃን መልአክ ቢሆን እንኳ፡ “የተረገመ ይሁን” ብሏል። አሁን፡ ብዙ ጥሩ ነገሮች አሉ። እኔ... እኔ ይህንን ርዕስ... ለሰዎች ለማድረስ የመረጥኩት፡ ሁለት ቀናትን ብቻ ናቸው። እነርሱም ትላንትና፡ እና የዛሬ ከሰዓት ስብሰባዎች ናቸው።

30 አሁን፡ ይህን ያደረግኩበት ምክንያት፡ እግዚአብሔር እንደሚረዳኝ ለማየት ራሴን ትንሽ ለመሞከር ነው። በልቤ ላይ የሆነ ነገር አለ። እናም ይህ፡ ያ፡ ከዚህ ታላቅ መልእክት በኋላ፡ እኔም የተናገርኩት እውነት መሆኑን፡ እግዚአብሔር ራሱ በቃሉ፣ በመጀመሪያ፡ በቃሉ፡ ከዚያም በምልክቶች እና ድንቆች አረጋግጧል። አሁን፡ እኔ እንደማስበው፡ ከወንጌል እውነት ጋር ለቤተክርስቲያንቷ፡ ይህንን ወደ ቤተክርስቲያን ለማምጣት፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ግዴታ አለብኝ። በትክክል። ይህም ስህተት እስኪመሰል ድረስ፡ በብዙ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ፡ ተከፋፍለዋል። እንደው፡ ተመልከቱ፡ ዳግመኛ ስንወለድ ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን። ስለዚህ እውነታው፡ እግዚአብሔር እኛ የእርሱ ልጆች መሆናችንን እንድናውቅ ይፈልጋል ነው።

31 አሁን፡ የሰለሞን ቤተመቅደስ፡ ከመላው ዓለም፡ የተፈለፈለ መሆኑን አስታውሱ። አንድ ድንጋይ **በዚህ** አቅጣጫ፡ ሌላ ድንጋይ **በዚያ** አቅጣጫ፡ ሌላ ድንጋይ **በዚህ** አቅጣጫ፡ ሌላ ድንጋይ ደግሞ **በዚያ** አቅጣጫ ሁሉም የየራሳቸው መልክ ነበራቸው፡ ሁሉም አንድ ላይ ሲሰበሰቡ፡ ግን፡ የመጋዝ ድምጽ ወይም፡ የመዶሻ ድምፅ አልነበረም፡ ሁሉም ነገር ወደ ቦታው ተሰካካ። መሪውም እግዚአብሔር ራሱ ነበር።

32 እግዚአብሔር አሴምብሊስ የሚባል ቤተ ክርስትያን አለው፡ ሌላውም ቸርች ኦፍ ጋድ፡ አንዱ **ይህ**፡ አንዱም **ያ** ናቸው። እና፡ ሁሉም አንድ ላይ ሲሰባሰቡ፡ ግን፡ በወንድማማችነት ፍቅር አንድ ትልቅ ቡድን ይሆናሉ፡ እግዚአብሔርም ቤተክርስቲያኒቱን አንድ ላይ ሰብስቦ ወደ ሰማይ ይወስዳታል።

33 እያንዳንዱ ታዋቂ ሰዕል፡ በሥነ ጥበብ አዳራሽ ውስጥ ከመሰቀሉ በፊት፡ አስቀድሞ፡ በተቺዎች አዳራሽ ውስጥ፡ ማለፍ ግድ ነው። የጌታ እራት፡ የሳለ ሰው... ? ... ፡ ወይም፡ ይቅርታ አርጉልኝ፡ ስሙን አላስታውሰውም፡ ለማንኛውም፡ የሕይወቱን ዋጋ አስከፍሎታል። ያንን ሰዕል ሳለ። ክርስቶስን እና ይሁዳን በመሳል መካከል፡ ሀያ ዓመት ወይም፡ አሥር ዓመት፡ ገደማ የፈጀበት ይመስለኛል። በዚያ በታዋቂው ምስል ላይ፡ የክርስቶስ ገጽታ ወክሎ የሰራው ሰው፡ ከአሥር ዓመት በኋላ፡ የይሁዳ ገጽታ እንደተላበሰ አስተውላችኋል? በትክክል። እንዲሁ ነው። ከታላቁ የኦፔራ ዘፋኝነት፡ የክርስቶስን ገጸ ባህርይ ለመያዝ፡ ከዚያም የይሁዳ ገጸ ባህርይ ለመላበስ፡ አሥር የኃጢአት ዓመታት። አሥር ዓመትን መውሰድ አያስፈልጋችሁም። አሥር ደቂቃ ይወስዳል፡ ተመሳሳይ ነገር ይሆንላችኋል። በኃጢአት፡ ባሕርያችሁን ይቀይረዋል። ነገር ግን፡ ለማነኛውም፡ ይህ ምስል በተቺዎች ሁሉ አለፈ።

34 እኔም ስለ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፡ ስለ ተጠራው መንጋ እንዲህ አስባለሁ። መልካም፡ ይህንን ስናገር ማንንም ለመኮነን አይደለም። ሰባት ባህሮች ተሻግሬያለሁና፡ አሁንም ዓለምን ሦስተኛ ጊዜ ለመዞር ጉዞ ላይ ነኝ፡ ሰዎችም "ሆሊ-ሮለር! ሆሊ-ሮለር!" ይላሉ፡ እኔም በዓለም ዙሪያ ፈልጌ፡ እስካሁን አንድም ሆሊ-ሮለር አላገኘሁም። ይህ ስም ዲያብሎስ በህዝቡ ላይ የለጠፈው ስም ነው። ያ ነው በቃ። ሆሊ-ሮለር የሚባል ነገር የለም። እና አሉ ከተባሉት ሰድስት መቶ ሰልሳ-ሰምንት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መካከል መረጃ አለኝ፡ በዓለም ላይ ከተደራጁት፡ ከነዚህም ውስጥ ሆሊ ሮለር የተባለ አንድም የለም። ያም ከመንግስት ነው። እኔ የማውቀው አንድም ሆሊ ሮለር የሚባል ቤተ ክርስቲያን የለም። ስለዚህ፡ የዲያብሎስ አጠራር ነው። አሁን፡

ግን፡ በእነዚህ ሁሉ፡ ነገሮች ውስጥ፡ እግዚአብሔር አንድ ምስል ሰሏል። እነዚህ ምስኪን የቆዩ አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ወቅት እዚህ ነበሩ፡ አንዳንዶቻችሁ...

35 እነዚያን የሸበቱ-ሰዎች እመለከታቸዋለው። ትናንትና፡ ልጄን፥ በክፍሌ ውስጥ፡ እያጠናሁ ሳለሁ፡ አንድ አገልጋይ መጥቶ "ከአባትህ ጋር እጅ መጨባበጥ እፈልጋለሁ፡" አለው። እርግጥ ነው፡ ልጄ ያደገው ከነ ወንድም ባክስተርና ከሌሎች ጋር ስለሆነ፡ በእነርሱም ዘንድ፡ ወድያውኑ፡ "አይቻልም፡" ነው። ያንን አልወደውም። አያችሁ? ምንም ይሁን ምን... እርግጥ ነው፡ የሰው፡ እና የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን አልችልም። ይሁን እንጂ ከወንድሞቼ ጋር እጅ መጨባበጥ እወዳለሁ። ይህን ማድረግ እወዳለሁ። በዚያም የተለየ ነገር አለ፡ የ—አገልጋይ እጅ መጨበጥ እወዳለው። አገልጋይ ብቻ ሳይሆን፡ ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፡ መጨበጥ እወዳለው። በኋላ ባለቤቴ ስለነገረችኝ እንጂ እስከዚያ ሰዓት ድረስ አላውቅኩም ነበር። እንግዲህ፡ ያንን አገልጋይ እንዲህ ብሎት ቢሆን ይሻል ነበር፡ "አንድ ደቂቃ፡ ከኋላ እየጸለየ ነው፡ እ—እና ምን እንደሚል አያለው።" መልካም፡ ያ፡ ያ የተሻለ ነበር። ስለዚህ ያንን ላለማድረግ፡ ትንሽ እርማት ሰጠሁት። አያችሁ?

36 ስለዚህም እውነት ነው፡ ቅድም ወንድማችን እንደተናገረው፡ ልክ ላትሆን ትችላለህና። ይህን ከፈለጋችሁ ግን፡ ማታ—ማታ ላይ እጅግ ይደክመኛል፡ አያችሁ። ሰዎች ያነጋግሩኛል፡ ምናልባትም እያንዳንዳቸው በሽታ ይኖራቸዋል፡ እና ስለዚህ ጉዳይ ማውራት ሲጀምሩ፡ ወድያውኑ፡ ስለ ጉዳያቸው የሚነግራቸው የእግዚአብሔር መልአክ በዚያ ይገኛል።

37 አሁን ራሱ ቁጭ ብሎ፡ እያየኝ ያለ ሰው አለ፡ ይህ ሁሉ እውነት እንደሆነ ያውቃል፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ወይም ከአንድ ሰዓት ተኩል በፊት የሆነ ነገር ነው። ይህች እዚህ የተቀመጠችው እመቤት፡ በቀደም ምን እንደሆነ አላወቀችም፡ የእግዚአብሔር መልአክ በቀደም ማታ ላይ አንድ ነገር ተናገራትና፡ ነገሩ ሊገባት አልቻለም። ነገር ግን ዛሬ ተፈጸመ፡ ስለዚህ የተናገራት ነገር አሁን ምን ማለት እንደሆነ አውቃለች። ይገርማል፡ ቆሜ ከእሷ ጋር ስነጋገር፡ የጌታ መልአክ ወዲያውኑ ወደ ኋላ ሄደ ምን ችግር እንደገጠማት፡ ሁሉም ነገር ምን እንደሆነና፡ ም—ምን እያሰበች እንደሆነ፡ የምትወዳቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ፡ እግዚአብሔር እንዴት እንደተናገረና እንዳረጋገጠላት፡ እና ምን ሊከሰት እንደሚችል ነገራት። ስለዚህ በትክክል እሱ እንደተናገረው ይሆናል። አያችሁ? እግዚአብሔር ተናግሯልና።

38 እንግዲህ አሁን፡ ይህ ነገር ጥቂት ጊዜ ከተደጋገመ... ወድያውኑ፡ እያንዳንዱ ራእይ እጅግ ያዳክማችኋል፡ አያችሁ። ስለዚህ ማታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትገቡ፡ የመጀመሪያ ነገር የምታውቁት፡ ምን ማድረግ እስከማታውቁ ድረስ ፈጽማችሁ መድከማችሁ ነው። አሁንም ጸልዩልኝ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም ከአንድ ሰብሰባ ወደ ሌላ፡ ከዚያም ወደ ሌላ ነውና። ከሁሉም የተለየ ጉባኤ የሚሆነው፡ ይህ ብቻ ነው፡ አሁን ወደ ቤት ሄጄ ለጥቂት ወራት ምንም ነገር የማላደርግ ከሆነ፡ ወጥቼ የአሳ ማጥመጃ ገመዴን አመጣና ወደ ዓሣ ማጥመድ እሄድ ነበር። ነገር ግን ከአንዱ ሰብሰባ በቀጥታ ወደሌላው መሄድ አለብኝ፡ ከአንዱ በቀጥታ ወደሌላው፡ አያችሁ። ነገሩ ይህ ነው።

39 እናንተ እዚህ ከጉባኤው ያላችሁ ሰዎች፡ ሁላችሁም ጸልዩ። ትናንት

ማታ ከ—ከአንድ ሰው ጋር እየተነጋገርኩ ነበርና፡ ግለሰቡ ለጥሪው ምላሽ እንዳልሰጠ ነገሩኝ። አሁን፡ ይህ ደግሞ በጣም አደገኛ ነገር ነው፡ እያችሁ። እነሱ ሲናገሩ... መልካም፡ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ መብራቶች ቦግ አይሉም፡ በመካከላቸው ጨለም ያለ ነገር ይኖራል።

40 የጌታን መልአክ እዚህ ሲቆም እመለከታለሁ፡ ስሜቱ አይሰማኝም። ከዚያም ከኔ ሲርቅ ይሰማኛል፡ እኔም እመለከታለሁ፡ ትቶኝ ይሄድና ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል እና እዚያ ትንሽ ይቆማል፡ እኔም ማየት እችላለሁ። እሱም ያበራል እናም ራእይ ይመጣል። ከዚያም እኔ ራዕይ እያለው። በዚያ ዙሪያ ምን ምን አይነት ሰው እንዳለ እመለከታለው። ሰውየው አገኘዋለሁ፡ ከዚያም አነጋግረዋለሁ። የሚሆነው ይህ ነው። የሚሆነው ይህ ነው። ይህም ለሁሉም ሰው መናገር አይጠበቅባችሁም፡ የሚሆነው ግን—ያ ነው፡ እያችሁ። ሁሉም በመንፈሳዊው ዓለም ዘንድ ነው።

41 ከዚያም ይህ ሰው ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ፡ መጽሀፍ ቅዱስ ሲነበብ እንደሚለው ይሁን፡ “ምንም ሳትሉት፡” ከእሱ ራቁ። እያችሁ? ያን ጊዜ የከፋ ይሆናል። ስለዚህ ንቁዎች ሁኑ፡ አዳምጡ፡ ተመልከቱ። ሲናገራችሁ፡ መልሱ። እያችሁ፡ በቃ በማንኛውም ጊዜ ለመመለስ የተዘጋጃችሁ ሁኑ።

42 ስለዚህም ባለቤቴና፡ ወንድም ቢለር ሌሎችም ብዙዎቹ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ስለ ጉዳዩ እየነገሩኝ ነበር፡ ይህ ሰው ስለ ወንድሙ እየተጠራ ነበር፡ በሆነ ነገር ላይ፡ ከሱ ጋር በሆነ ችግር ውስጥ ገብተው ስለ ነበር፡ ወዘተረፈ። ሰውዬውም ለጥሪው መልስ አልሰጠም፡ ስለዚህ መፍትሔ እያገኝም። ያም በእግዚአብሔር እና በሰውዬው መካከል ነው። ራእዩ ተለይቶኝ ሄደ። ከዚያ በኋላ መልስ ስላልሰጠ፡ ማግኘት አልቻልኩም። ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ ንቁዎች ሁኑ።

43 አሁን ይህን ርዕስ **አጋንንት** በተመለከተ ወስደን ስለ አጋንንት እንናገራለን። አሁን፡ “አጋንንት” ስትሉ፡ ሰዎች፡ ወዲያውኑ ማሰብ የሚጀምሩት፡ “ኡህ፡ የሆነ አክራሪነት ወይም ሌላ ነገር ነው!” ነገር ግን አጋንንት ልክ እንደ መላእክት ናቸው። ልክ እንደ መላእክት እውን ናቸው።

44 ዲያብሎስም ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነው ሁሉ፡ ዲያብሎስም እውን ነው። ዲያብሎስ ነው! ገነትም እንዲሁ እውን ነው። ገሃነም የሚባል ነገር ከሌለ፡ ገነት የሚባል ነገር አይኖርም። ዘለአለማዊ በረከት... ማለቴ፡ ዘላለማዊም ቅጣት ከሌለ፡ ዘላለማዊ በረከት የለም። ቀን ከሌለ፡ ሌሊትም አይኖርም። እያችሁ? ቀን እንዳለ ሁሉ ግን፡ ሌሊት ደግሞ አለ። ክ—ክርስቲያን እንዳለው ሁሉ፡ ግ—ግብዝም ሊኖር እንደሚችል የታወቀ ነው። በእውነት ከእግዚአብሔር የሆነ ሰው እንዳለ፡ ያንን አስመሳይ ሰው ደግሞ አለ። እያችሁ? ሁሉም ነገር በጥሩና በመጥፎ፡ በጥቁር እና በነጭ፡ በሕይወት ውስጥ በሁሉም ነገር፡ በሁሉም ቦታ እውነትና ሐሰት ነው። እና ሐሰተኛ ወንጌል አለ፡ እውነተኛ ወንጌል አለ። እውነተኛ ጥምቀት አለ፡ ሐሰተኛ ጥምቀት አለ። አስመሳይ-እምነት አለ፡ እውነተኛው እምነት አለ። እውነተኛ የአሜሪካን ዶላር አለ፡ የውሸት የአሜሪካን ዶላር አለ። እውነተኛ ክርስቲያን አለ፡ የተገለጠ ግብዝ አለ፡ እያችሁ፡ ይህም አስመሳይነት ነው። ስለዚህ ይህን ተረዱ፡ ሁሉም አብሮ የሚጓዝ ነው። አሁን፡ ልንለያቸው አንችልም። እግዚአብሔር ዝናብ እንዲዘንብ ያደርጋል።

45 በዚህ ላይ ትንሽ እንድናገር ፍቀዱልኝ። ስንት ሰባኪዎች አላችሁ? እጃችሁን እንሡ። ሁላችሁም እዚህ ያላችሁ፡ ሰባኪዎች፡ እጃችሁን እንይ። መልካም፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ወንድሞቼ። አሁን፡ አሁን፡ ይህንን አሁን እንደ ዶክትሪን አትውሰዱ፡ ነገር ግን፡ ወደዚህ ወሳኝ ርዕሰ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት፡ አንድ ነገር እነግራችኋለው። እስኪ ስንት የጴንጤቆስጤ ሰዎች አላችሁ? በዙሪያው በሁሉም ቦታ ያላችሁ፡ እጆቻችሁን እንሡ። መልካም፡ ሁላችሁም የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታዮች ናችሁ። ደኅና። ወደ እናንተ ለመጀመሪያ ጊዜ ስመጣ የነበረኝ ነገር፡ ላጫውታችሁ እፈልጋለሁ።

እዚህ ኢንዲያና ውስጥ፡ ሚሻዋካ በሚባል አንድ ቦታ ነበርኩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋቸው የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ ይመስለኛል—ፔንቴኮስታል አሴምብሊስ ኦፍ ጂሰስ ክራይስ፡ ወይም ሌላ ነገር ተብለው የሚጠሩ፡ ይመስለኛል፡ ድንቅ ሰዎች ናቸው። አሁን ላይ በአንድነት ተደራጅተው የተባበሩት ጴንጤቆስጤ ተብለው ይጠራሉ። ከሌሎቹ የተለያዩት፡ በውኃ ጥምቀት ምክንያት ነው። ይህን ማድረጋቸው ግብዞች አያሰብላቸውም። በመካከላቸው ብዙ እውነተኛ፡ በእውነተኛ መንፈስ ቅዱስ፡ ዳግመኛ-የተወለዱ ክርስቲያኖች አሉ። እግዚአብሔርም “በኢየሱስ ስም” በመጠመቃቸው መንፈስ ቅዱስን ሰጣቸው፡ ሌሎቹንም “በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ” በመጠመቃቸው የመንፈስ ቅዱስን፡ ጥምቀትን ይሰጣቸዋል። ስለዚህ፡ “እግዚአብሔር ለእርሱ ለሚታዘዙት፡ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸዋል፡” ስለዚህ ማ—ማን ያገኛል፡ እርሱን የታዘዘው? እንግዲህ ይኸውላችሁ።

46 ብቻ እርሱት፡ እንዲህ መሆን እንፈልጋለን ያሉትን፡ ተዉቸው ይሁኑ፡ የራሳችሁን ቀጥሉና ወንድማማቾች ሁኑ። በቃ። እንዲህ አይሁን… ያንን ያደረገው፡ መለያየት፡ መበታተን ነው። አያችሁ? ምን? መፍረስ፡ መበታተን፡ ከወንድማማችነት መለያየት፡ ራስን ለይቶ መውጣት ነው። አይ፡ ወዳጄ፡ የተለያየን አይደለንም፡ አንድ ነን። ያ ትክክል ነው።

47 ነገር ግን እዚያ ቆሜ፡ ሰዎቹን እያየኋቸው ነበር። እንግዲህ፡ እኔ፡ ከመደበኛዋ ሳውዘርን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን የመጣ ሰው ነበርኩ፡ ለምን፡ እነዚያን ሰዎች ለማየት፡ ወደዚያም ገባሁ እና እያጨበጨቡ፡ እየዘመሩም ነበር፡ “አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ!”

48 ሲዘምሩ እንዲህ አሰብኩ፡ “ማይ! ዋው!” ታውቃላችሁ የመጀመሪያው ነገር፡ በዚህ በኩል አንድ ሰው፡ መደነስ በሚችለው ሁሉ እየደነሰ መጣ። “ቱህ-ቱህ-ቱህ-ቱህ-ቱህ፡” ሲል “እንዴት ያለ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው! እንደዚህ አይነት ነገር ሰምቼ አላውቅም፡” አልኩ። በየቦታው፡ እየተመለከትኳቸው ነበር። “እንዴ፡ ምን ጉድ ፈላባቸው እነዚህ፡” ብዬ ራሴን ጠየኩ?

49 አሁን፡ በዚያ ስብሰባ በተሳተፍኩ ጊዜ፡ በሕይወት ታሪኬ ስናገር ሰምታችኋል። ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት፡ አደባባይ ላይ ተናግሬው የማላውቅ፡ አንድ ነገር አለ። እነርሱም… አሁን፡ ይህንን ከድምፅ መቅጃዎች ላይ ማጥፋት ከፈለጋችሁ፡ ታዲያስ፡ ማድረግ ትችላላችሁ። መልካም። አሁን፡ በዚያ ውስጥ ሳያቸው፡ “እንግዲህ፡ እነዚህ ሰዎች በሕይወቴ ውስጥ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ በጣም ደስተኛ ሰዎች ናቸው፡” ብዬ አሰብኩ። በሃይማኖታቸው አያፍሩም። እኛ ባፕቲስቶች አንድ አንድ ጊዜ፡ ትንሽ እናፍራለን፡ ታውቃላችሁ። አያችሁ?

ለመጸለይ ሲሄዱ፡ ታውቃላችሁ፡ ከሸንትለተሩ በስተጀርባ ተደብቀው ነው፡ ታውቃላችሁ። እ—እና፡ እነዚያ ሰዎች ግን... አያፍሩም ነበር፡ ወንድሜ፡ ሁሉም በ—በውስጣቸው፡ በውጪያቸው፡ በዙርያቸው ሁሉ ላይ ሃይማኖት ነበራቸው።

50 መልካም፡ በዚያ ምሽት ወደ መድረክ ሰወጣ አስታውሳለው። “ሰባኪዎች የሆናችሁ ሁላችሁ ወደ መድረክ ውጡ፡” አሉ። ኮንቬንሽን ነበር። እዚህ ስሜን ውስጥ የተደረገበት ምክንያት፡ የቀለም ዘረኝነት ሰለ—ነበረ ነው፡ በደቡብ በኩል የጂም ክሮው ሕግ ነበርና። ስለዚህ ሁሉም ከየቦታው እዚያ ተሰብሰበው ነበር። ስለዚህ፡ እኔም በዚያ ተቀምጬ ነበር። እንዲህ አለ... በዚያም፡ እንግዲህ... የቀን እና የማታ ሰባኪዎች ሁሉ ሰምቻለሁ። የሆነ ሽማግሌ ሰባኪ ጠሩት፡ ሽምገል ያለ ጥቁር ሰው መጣ፡ በራሱ ጠርዝ ላይ ትንሽ ጸጉር የቀረለት ሰው፡ ልክ **እንደዚህ፡** ትልቅ ፍሮክ-ቴይልድ የሰባኪ ካፖርት ለብሷል፡ ታውቃላችሁ፡ ቬልቬት አንገትጌ አድርጎ፡ ወደ መድረክ መጣ። ምስኪን ሽማግሌ ሰውዬ **እንደዚህ** ወደ መድረክ መጣ። እንዲህ አለ፡ “ልጆቼ ሆይ፡” አለ፡ “ልነግራችሁ እፈልጋለው፡” መመሰከር ጀመረ። በሰብሰባው መድረክ ላይ ከተቀመጡት በእድመ ትንሹ እኔ ነበርኩ ማለት ይቻላል። ስለዚህ እንዲህ አለ፡ “እነግራችኋለው!” ጥቅሱን ከእዮብ ወሰደ፡ “እኔ የዓለምን መሰረት ሰጥል አንተ የት ነበርህ? በምን ላይ እንደጸኑ ተናገር።”

51 እነዚህ ሁሉ ሰባኪዎች በመደበኛው መንገድ፡ ሰለ ክርስቶሰ ይሰብኩ ነበር። አዳመጥኳቸው፡ ተባርኬበታለሁ። ሽማግሌው ግን እንደዛ አይደለም! ዓለም ከመፈጠሩ አሥር ሺህ ዓመታት በፊት ወደ ኋላ ተመለሰ። ወደ ሰማይ ወጣ በሰማያት በኩል ወደ ታች ወረደ፡ የሆነው ነገር ይህ ነበር። እነርሱ በቀን ውስጥ፡ ምን እየተከናወነ እንዳለ፡ ይሰብኩ ነበር፥ እርሱ በሰማይ ምን እየተከናወነ እንዳለ ይሰብክ ነበር። እርሱ ክርስቶስን ወደ ዘላለማዊነት፡ በአግድም ቀስተ ደመና አመጣው። ለምን፡ ሽማግሌው ገና አምስት ደቂቃ እንኳን ሳይሰብክ፡ የሆነ ነገር ወረደበት። በአየር ላይ ዘለለና የጫማ ተረከዞቹን አንድ ላይ አጋጫቸው፡ እና “ዉፒ፡” ብሎ ጮኸ! ለእኔ እዚህ ያለኝ የሚያክል ክፍት ቦታ ነበረው። “እኔ የምሰብክበት በቂ ቦታ የላችሁም፡” አላቸውና፡ እንዲህ ሄደ።

52 እኔም፡ እንዲህ ማሰብ ጀመርኩ፡ “ይህ የሰማንያ አመት የሞላውን አዛውንትን እንደዛ ካደረገው፡ እኔን ምን ያደርገኛ ይሆን? እኔ የምፈልገው ያንን ነው። እኔ የምፈልገው ያንን ነው።”

53 ከሁሉ የገጠመኝ ነገር ግን ይህ ነው። አሁን፡ ሰለ አጋንንት እያወራን ነው። ያጋጠመኝ፡ ሁለት ሰዎችም አየሁ። አንደኛው በአንድ በኩል፡ ሌላኛው በሌላ በኩል ተቀምጠዋል። መንፈስ ሲወርድም፡ ሁለቱ ሰዎች ተነሥተው የአፋቸው ዙሪያ ነጭ እስኪሆን ድረስ ይጮኻሉ፡ በልሳኖችም ይናገሩ ነበር። “ኦህ፡ ማይ፡ እኔም ይህን በኖረኝ ኖሮ!” ብዬ አሰብኩ፡ አያችሁ? “እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው! ኦህ፡ ያ... በቃ ደስ አለኝ!” ከዚያ፡ ወደ በቆሎ መስክ ወጣሁ። የሕይወት ታርኬን ነግሬያችኋለሁ። ከመጽሐፉ አንብቡት። ሌሊቱን በዚያ አሳለፍኩት። ስለዚህ እስኪ ልፈትናቸው ብዬ፡ በሚቀጥለውም ቀን በጠዋት ተመልሺ መጣሁ። ከእኔና ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የማያውቀው ነገሮችን የማደርግበት አንድ ነገር አለኝ። ስለዚህ፡ አንድ ነገር እንቆቅልሽ ከሆነብኝ፡ የሰው መንፈስ ለመገናኘት እሄዳለሁ። እዚህ በመድረኩ ላይ ታዩታላችሁ። አይደል? ከዚያም

ከሰዎቹ አንዱን ማነጋገር ጀመርኩ። አንድ ላይ ተቀምጠው፡ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲጨፍሩና፡ ሲጮኹ አየሁ። “ኦህ፡ ማይ፡ ይህ ለእኔ እውን ነው!” ብዬ አሰብኩ፡

54 እኔም የአንዱን እጁን ያዝኩ። “ጤና ይስጥልኝ፡ ጌታዬ፡” አልኩት?

55 እርሱም “ጤና ይስጥልኝ፡” አለኝ። በጣም ጥሩ ሰው ነህ፡ ጨዋ-ሰው ነው። እርሱም… .

“አገልጋይ ነህ፡” ጠየቅኩት?

እርሱም “አይ፡ ጌታዬ። እኔ ተራ አባል ነኝ፡” አለኝ።

56 ስለዚህ መንፈሱን መያዝ እችል ዘንድ ከእርሱም ጋር ትንሽ መነጋገር ጀመርኩ። አያችሁ? እሱ አያውቅም። ማንም አያውቅም። ለማንም ተናግሬ አላውቅም። ሳልናገር፡ ብዙ ዓመታት አልፏል። ስለዚህ… ለማወቅ በመጣው ጊዜ ግን፡ እንደ እውነተኛ፡ ክርስቲያን፡ ፍጹም ሆኖ አገኘሁት! ይህ ሰው ፍጹም የእግዚአብሔር ቅዱስ ሰው ነበር። እኔም “ጥሩ ነው፡ ወንድሜ፡” ብዬ አሰብኩ።

57 ነገር ግን እንግዳው ነገር፡ ሌላኛውን ሰውዬ ባነጋገርኩት ጊዜ ግን፡ ተቃራኒ ነበር። ይህ ሰው ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር አብሮ ይኖር ነበር። በእውነት። ወደ እርሱም በቀረብኩ ጊዜ፡ ራእይ አየሁ። “ኦህ፡ ማይ፡ እንደዚህ ሊሆን አይችልም፡” ብዬ አሰብኩ። ይህ ሰው… አልኩ፡ “አሁን፡ አሁን፡ በእነዚህ ሰዎች መካከል ያለው መንፈስ የተሳሳተ ነው። ችግር አለበት አልኩ።”

58 በዚያ ምሽት… ወደ ስብሰባው በሔድኩ ጊዜም፡ በረከቶቹ በጉባኤው ላይ ሲፈሱ ነበር፡ ወደ እግዚአብሔርም ጸለይኩ፡ መንፈስ ቅዱስም፡ የሚወርደው እውነተኛ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን የጌታ መልአክ መሰከረልኝ። **በዚህ** ሰው ላይ ይወርድ የነበረው ያው መንፈስ **በዚያ** ሰው ላይም ደግሞ ይወርድ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ሲወርድም፡ ሁለቱ ይነሱና፡ ሁለቱም በታላቅ ድምጽ እየጮኹ ጌታን ያወድሳሉ፡ በልሳኖችም ይናገራሉ ያሸበሸባሉ። እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ ይ—ይህ ሊገባኝ አ—አልቻለም አልኩት። በ… በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ይህ ነገር ትክክል እንደሆነ ማየት አልቻልኩም።” አሁን “ምናልባት ተታልየ ይሆናል፡” አልኩ። አያችሁ? አ… አሁን፡ እዚህ ላይ፡ አ—አልደራደርም… በ—በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወግ አጥባቂ ነኝ። ይህ መሆን አለበት። አያችሁ? እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ ያለሁበትን ሁኔታ ታውቀዋለህ፡ በ—በቃልህም በኩል ማየት አለብኝ። ይሄን መረዳት አ—አልቻልኩም። መንፈስ ቅዱስ **በዚኛው** ሰውዬ ላይ ሲወርድ፡ ያው መንፈስ ቅዱስ **በዚያኛው** ሰውዬ ላይም ይወርዳል፡ አንደኛው ቅዱስ ሌላኛው ደግሞ ግብዝ ነው። እንደዛ እንደሆነም አውቄአለሁ።” አውቃለው። ሰ… ሰውየውን ውጪ አውጥቼ ላረጋግጥለት እችል ነበር፡ ወይም ባለበት ጠርቼ ስለዚህ ነገር እነግረው እችል ነበር።

59 ልክ እንደ ትናንት ማታ እዚህ ተቀምጦ እንደ ነበረው ሰውዬ፡ እርሱ አለ የተባለ—ሀሰተኛ ሰው ቢኖር፡ ከርሱ ሌላ እምነት የለም። ከጉባኤ ውስጥ መጥራት እችል ነበር፡ ነገር ግን ተነሥቶ መጨቃጨቅ ስለሚጀምር ተውኩት። ስለ በስብሰባው ብዬ፡ ተውኩት፡ ነገር ግን አውቄው ነበር። አዎን፡ ወዳጄ።

በቀደም ምሽት፡ በከተማችን የአንድ ቤተክርስቲያን አባል የሆኑ፡ ሁለት ሰዎች፡ እዚህ፡ ከኋላ ተቀምጠው ነበር። በጣም አቃቂራሞች ናቸው! አይቻቸዋለሁ። የሆነ ነገር ብትሏቸው፡ ግን፡ በቃ ችግር መፍጠር ይጀምራሉ።

ብዙ ጊዜ ሞክሬዋለሁ። እንዲሁ እተዋቸዋለሁ፡ አያችሁ። ምንም ችግር የለውም። ፈራጁ እሱ እንደሆነ፡ እግዚአብሔር ያውቃል። አንድ ጊዜ ብቻ ይጥሩኝና፡ ከዚያም የሚፈጠረውን ታያላችሁ፡ አያችሁ፡ ተውት።

ልክ እንደ አጋንንቱ፡ አጋንንቱን በጭራሽ አልጠራሁትም። ራሱ ወደ እኔ መጣና ተገዳደረኝ። እግዚአብሔር ሥራውን የጀመረው ያን ጊዜ ነው፡ አያችሁ፡ ትክክል ነው፡ ምን እንደሆነም አይታችኋል። በቃ። እኔ ግን ዝም አልኩት። ስብሰባውን አስቸጋሪ እንዲሆን አደረገው፡ ይህ መንፈስ ሁል ጊዜ ያስጨንቀኝ ነበር፡ አያችሁ። እኔም ዝም ብዬ እቀጥላለው።

60 አሁን ግን፡ እነዚህ ሰዎች፡ ሊገባኝ አልቻለም። በግሪን ሚል፡ ኢንዲያና፡ እዚህ፡ በሰካውት ሪሰርቨሽን ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ፡ ከሁለት፡ ወይም ከሦስት ዓመት በኋላ ነበር። ለመጸለይ በምሄድባት ዋሻ ውስጥ ነበርኩ። እዚያም፡ እንዲህ አልኩ፡ "ጌታ ሆይ፡ የዚያ ቡድን ሰዎች ምን እንደሆኑ አልገባኝም። በሕይወቴ ካገኘኋቸው ምርጥ ሰዎች አንዱ ናቸው፡ ይህ እንዴት የ—የተሳሳተ መንፈስ ሊሆን እንደሚችል አልገባኝም። የ... የልቤን... ቅንነት አንተ ታውቃለህ። ምን ያህል እንደምወድህ እና እንዴት እንዳገለገልኩህ ታውቃለህ። እዚህ፡ ከእኔ ጋር ያለው መንፈስ፡ በእነዚያ ሰዎች ላይም ነበር። እነሆ፡ በአንደኛው ሰውዬ ላይ፡ የነበረው መንፈስም ያው ነበር።" ስለዚህ ሊገባኝ አልቻለም።

61 ጌታም በምሕረቱ መጣና አሳየኝ። እዚህ ጋር ነበር። በመጀመሪያ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለበት። "መጽሐፍ ቅዱስህን አንሣ፡" አለኝ። እኔም መጽሐፍ ቅዱሰዬን አነሳው። ይመስለኛል ለአሰር ደቅቃ ያህል ምንም ቃል... ሳየመጣ መጽሐፍ ቅዱሱን ይዤው ቆየሁ። ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ጠበቅኩት። "ዕብራውያን ምዕራፍ 6 ከፍተህ ማንበብ ጀምር፡" ሲል ዳግመኛ ሲናገር ሰማሁ። እኔም አነበብኩት። ወደ ታች እያነበብኩ፡ እንደዚህ የሚል ቦታ ደረሰኩ፡ "ዝናቡም ብዙ ጊዜ ወደ ምድር የሚመጣው ለማጠጣት ለማዘጋጀትና፡ ለማስታጠቅ ነው... እሾህና ኩርንችትን ግን ብታወጣ፡ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፡ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።" ነጥቡን እዚያ ጋር አገኘሁት።

እኔም፡ "ይኸው። እግዚአብሔር ይመስገን! ይኸው ነው" ብዬ አሰብኩ። አያችሁ?

62 አሁን፡ ኢየሱሰ እንዲህ አለ፡ "ዘሪ ዘር ሊዘራ ወጣ፡" አላለም ወይ? አሁን፡ ሁላችሁም ክርስቲያኖች ናችሁ። የጴንጤቆስጤ፡ ዳግም-የተወለዳችሁ ክርስቲያኖች፡ የሆናችሁ፡ ሁላችሁ እጃችሁን አንሱ። እሺ። እ... እንዲህ አለ፡ "ዘሪ ዘር ዘርቶ፡ ሄደ። እርሱም ተኝቶ ሳለ... " በዕረፍቱ፡ በሞቱ፡ መካከል። አያችሁ? "ተኝቶ ሳለ፡ ጠላት መጥቶ በእርሻው ላይ እንክርዳድ ዘራ።" እንክርዳድ ምንድን ነው? አረሞች፡ እሾህ እና ሌሎች ነገሮች ናቸው። አሁን፡ "ሰራተኛውም (ሰባኪው) እነዚህ እንክርዳዶች ሲበቅሉ ሲያይ፡ እንዲህ አለ፡ 'ልውጣና ልንቀላቸው' አለ። እርሱም፡ 'አይ፡ አይሆንም። ስንዴውንም አብረኸው ትነቅላለህ። ተዋቸው አብረው ይደጉ' አለው።"

63 እዚህ ጋር አንድ የስንዴ እርሻ አለ። በውስጡም አረጎች፡ ሳማዎች፡ ሸታ ያላቸው አረሞች፡ ሌላም ብዙ ነገሮች ሁሉ አሉበት። ልክ ነው? አሁን፡ በዚያ

ውስጥ ግን፡ ሰንዴ አለ። ስለዚህ፡ እሱን ለማጠጣት፡ ብዙውን ጊዜ ዝናብ ወደ መሬት ይዘንባል። አሁን፡ ዝናቡ ለምን ይመጣል? ሳማዎችን ለማጠጣት አይደለም። አሁን ተመልከቱ እና ትኩረት ሰጡ። አረሳቹን ለማጠጣት አይደለም። ዝናቡ የተላከው ለሰንዴው ነው፡ ነገር ግን ሳማ እና አረም ልክ እንደ ሰንዴው የተጠሙ ናቸው። በሰንዴ ላይ የሚወርደው ዝናብ በእንክርዳዱ ላይም ይወርዳል። ልክ ትንሹ ሰንዴ ወዲያውኑ እንደሚቆም ሁሉ፡ ትንሹ እንክርዳድም ልክ እንደዚያ ቀጥ ብሎ ይቆምና፡ ይደሰታል ሀሰት ያደርጋል።

64 "በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።" ይኸው። አያችሁ? ስለዚህ፡ ይህ ተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስ ግብዞችን ሊባርክ ይችላል። አንዳንዶቻችሁ አርሚኒያኖች ይህ ሊከብዳችሁ ይችላል፡ ይሁን እንጂ እውነት ነው። ይህ እውነት ነው። ቅድሰና ያስተምራሉ፡ እኔ ደግሞ፡ በቅድሰና አምናለሁ። ያው ተመሳሳይ መንፈስ፡ ተመሳሳይ ዝናብ በጻድቃንና በኃጢአተኞች ላይ ያዘንባል፡ ነገር ግን ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።

65 እዚህ ወጥቼ ሰንዴን ለመመልከትና ለማፈስ ሰወጣ፡ ሰንዴን አገኛለው፡ ነገር ግን አረሞች አንድ ላይ ተቀላቅለው ይገኛሉ። እነሱም ለሰንዴው በወረደ ተመሳሳይ ዝናብ ይኖራሉ። ዝናቡ የተላከው ለእንክርዳዱን ሳይሆን፡ ለሰንዴው ነው። ነገር ግን ዝናቡ በእርሻው ላይ በመሆኑ፡ እ... እንክርዳዱ በእርሻው ውስጥ በመሆኑ፡ ከዝናቡ ልክ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ጥቅም ያገኛል። እንዲሁም ሰንዴውን ሕያው የሚያደርግ ዝናብ፡ እንክርዳዱንም ሕያው ያደርገዋል።

66 በተፈጥሯዊ ነገሮች ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ፡ እኛ እንደምናስተምረው የመንፈሳዊ ጥላዎች ናቸው። ይኸውም፡ እነዚህ አጋንንታዊነት፡ ክርስትናን የሚያስመስሉ አጋንንቶች ናቸው፡ ሆኖም፡ በረከትን ያገኛሉ። ወንድሞቼ፡ ልትሸከሙት ከቻላችሁ፡ ይህ ቅባት የሌለበት ወተት አይደለም። አያችሁ? አያችሁ? አሁን፡ ይ—ይህ እውነት ነው።

67 ስለዚህ፡ ዛሬ መጮኽ ስለምችል አልዳንኩም። እንደዳንኩ ስለተሰማኝ አልዳንኩም። የዳንኩት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቅድመ ሁኔታዎችን ስለ አሟላሁ ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ "ቃሌን ሰምቶ የላከኝን የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሮአል እንጂ፡ ወደ ፍርድ አይመጣም።" ይህንን አምናለው። በትክክል። በእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ድኛለው፡ እግዚአብሔርም ተናግሯልና።

68 አንድ ሰው፡ "ኃይለኛ ነፋስ ፊትህ ላይ ሰለ ነፈሰ" ድነሃል ቢለኝ፡ ግሩም ነገር ነው። ነገር ግን ፊቴን ከመምታቱ በፊት ኃይለኛው ነፋስ ከየት እንደመጣ ማወቅ እፈልጋለሁ፡ አያችሁ። አሁን፡ ኃይለኛው ነፋስ ከመታችሁ በኋላ ምን ዓይነት ሕይወት ትኖራላችሁ? አያችሁ? አያችሁ፡ በፍሬያችሁ ትታወቃላችሁ። ስለዚህ፡ አጋንንቶች በክርስቲያኖች መካከል በትክክል መሥራት ይችላሉ። ታምናላችሁ? ጳውሎስን ተመልከቱት፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ...

69 የኋለኛው-ዝናብ ማለት ይህ ነው... እዚህ ያላችሁ ሁላችሁ፡ በእናንተ ላይ የተናገርኩት ነገር ካለ ይቅርታ አድርጉልኝ። በአሰምብሊስ እና በሌሎች፡ በባፒትስቶች፡ ወይም በሌላ፡ ከምናገረው በላይ በእናንተ ላይ አልናገርም። እውነቱ እውነት ነው። ስህተታችሁ፡ ይህ ነው፥ ከነዚህ ሰዎችና ነቢያት ካልሆኑ ሰዎች ነቢያት መሾማችሁ ነው። ነቢያት "እጅ በመጫን" አይሾሙም። ነቢያት

ይወለዳሉ እንጂ። አያችሁ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የትንቢት **ስጦታ** አለ። ስህተታችሁ እዚህ ጋር ነው፡ በትንቢት ስጦታና በነቢይ መካከል ነው። ስጦታ...

70 “እግዚአብሔር፡ በተለያየ ጊዜና በተለያየ መንገድ በነቢያት አማካይነት ለአባቶቻችን ተናገረ፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ደግሞ፡ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ተናገረ።” በክርስቶስ አካል ውስጥ ዘጠኝ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይሠራሉ። ትንቢት፡ ዛሬ ማታ **በዚህች** ሴት ላይ መጥቶ፡ ምናልባትም በቀሪው ዘመኗ ላይመጣ ይችላል። በቀጣይ ምሽት **በዚህች** ሴት ላይ ሊሆን ይችላል። ምናልባት በቀጣይ ጊዜም **በዚህ** ሰው ላይ ሊሆን ይችላል። በሚቀጥለው ጊዜ፡ **በዚያ** ላይ ሊሆን ይችላል። ይህ ግን ነቢይ አያደርጋትም፡ ማንንም ነቢይ አያደርግም። በውስጣችሁ ያለው የትንቢት ስጦታ ነው እንጂ።

71 እና ያ ሰው ወይም ትንቢቱ ለቤተክርስቲያን ከመሰጠቱ በፊት፡ በሁለት ወይም በሦስት መንፈሳዊ ዳኞች ፊት ሊዳኝ ይገባል። ልክ ነው? እንደ፡ ጳውሎስ መሰረት፡ እርሱ እንደተናገረው፡ “አንድ በአንድ፡ ሁላችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ” ብሏል። **ለዚኛው** አንድ ነገር ከተገለጠለት፡ **ያ** ዝም ይበል። እንግዲህ፡ በዛሬው ጊዜ ባለው ትምህርት አንጻር ቢመዘን፡ ያ ሁሉንም ነብያት ያደርጋቿል። አይደለም፡ የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን ሆይ፡ ሁሉንም ነገር አበላሽተናል። እግዚአብሔርም ወደ ውስጥ መግባት የማይችልበት ምክንያት፡ ይህ ነገር እስኪስተካከል እና በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት እስኪሆን ድረስ ነው። በትክክል። ትክክለኛውን መንገድ መከተል አለባችሁ። እቅዳችሁን ሳትመለከቱት ቤት ለመገንባት እንዴት ትሄዳልችሁ? አያችሁ? በትክክል መጀመር አለባችሁ።

72 አሁን፡ በዚያ ውስጥ፡ በነቢያት፡ በኢሳይያስ፡ በሙሴ በፊታቸው ማንም ሰው ቆሞ አላያችሁም። አንድ ቀን፡ ቆሬ፡ ቆሞ፡ ከእሱ ጋር ለመከራከር ሲሞክር፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ “ራስህን ላይ፡ መሬትን እከፍታለሁና... ” ነቢይ ይወለዳል። “ስጦታዎችና ጥሪዎች... -ንስሐ መግባት።” ከሕፃንነት ጀምሮ በእግዚአብሔር፡ አስቀድሞ የተወሰነ ነው። ሁሉም ነገር ፈጽሞ ትክክል ነበር፡ በትክክል የተናገረው ሁሉ እውነት እንደሆነ ተረጋግጦ ተገልጧል። የእግዚአብሔር ቃል የሚመጣው፡ ወደ ነብይ ነው። የትንቢት ስጦታ ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው።

73 አሁን እንዲህ ትላላችሁ፡ “መልካም፡ ነቢያት የብሉይ ኪዳን ናቸው።” ኦህ፡ አይደለም! በአዲስ ኪዳንም ነቢያት አሉ።

74 አጋቦስ የ—አዲስ ኪዳን ነቢይ ነበር። የትንቢት መንፈስ በላዩ ሲወርድና ስለ ጳውሎስ ሲናገር ተመልከቱ። ከዚያም አጋቦስ ከኢየሩሳሌም ወርዶ፡ ጳውሎስን አገኘውና፡ የጳውሎስን መታጠቂያ በወገቡ ታጠቀና፡ ዞሮ እንዲህ ሲል ተናገረ፡ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ የዚህ መታጠቂያ ባለቤት ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ በሰንሰለት ይታሰራል።” አጋቦስ፡ ተነሥቶ ተናገረ፡ ወደፊት የሚሆነውን ነገር ተነበየ፡ እርሱ ነቢይ ነበር እንጂ፡ የትንቢት ስጦታ ያለው ሰው አልነበረም።

75 የጴንጤቆስጤ ጓደኞቼ ሆይ፡ የፈወስ ስጦታ እና እነዚያ ሁሉ ስጦታዎችን፡ ቀላቅላችኋል። ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ፡ ወደ አካሉ በተጠመቀ በማንኛውም ሰው፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሰዎች ሁሉ

የሚገኙ ናቸው። "በአንድ መንፈስ ሁላችንም ተጠምቀናል።" መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል...

"እንግዲህ፡ እኔ ፈውስ ሰጦታ አለኝ።"

76 መልካም፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "እርስ በርሳችሁ ሃጥያታችሁን ተናዘዙ፡ አንዱም ስለ ሌላው ይጸልይ።" እያንዳንዱ ሰው ለሌላው ይጸልይ። እኛ የተከፋፈለ መንጋ አይደለንም፥ በአንድ ላይ፡ የተሰባሰበ መንጋ ነን። እያችሁ?

አሁንም፡ እንዲህ ነው አጋንንቶች አንዳንድ ጊዜ የሚሰሩት።

77 አሁን ጳውሎስ የተናገረውን ተመልከቱ፡ "አንድ ሰው በልሳን ቢናገር ሌላውም ቢተረጉመው፡ የሚናገረው ነገር ሁሉ፡ በቤተ ክርስቲያን ፊት ከመቅረቡ በፊት ለፍርድ ይቅረብ።"

78 እንግዲህ፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ብቻ፡ ወይም ሌላ ነገር አይደለም። እግዚአብሔር ራሱን አይደጋግምምና። ለቤተክርስቲያን ግን እንደ ማስጠንቀቂያ ነው። ከዚያም ዳኞች ከተናገሩ፡ "ይህን እንቀበለው።" መልካም፡ ይህ ትንቢት ከጌታ ዘንድ ነው ማለት ነው። ሁለተኛው "እንቀበለው፡" ይላል። "በሁለት ወይም በሦስት ምስክር፡ የአፍ ቃል ሁሉ ይጸናል።" ከዚያም ቤተክርስቲያን ያንን ትንቢት ትቀበላለች ለዚያም ትዘጋጃለች። ይህ በትንቢት የተነገረው፡ ካልተፈጸመ፡ በመካከላችሁ ክፉ መንፈስ አለ ማለት ነው። በትክክል። በትንቢት የተነገረው ከተፈጸመ፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በመካከላችሁ ነው። እያችሁ? አሁን፡ መመልከትና መጠንቀቅ ያለባችሁ እዚያ ጋር ነው። ስለዚህ፡ ለመጫን አትሞክሩ። ሰማያዊ አይን ካለኝ ቡናማ ዓይኖች እንዲኖረኝ ማድረግ አልችልም፡ እያችሁ፡ በሰማያዊ አይኖቼ መርካት አለብኝ። አሁን፡ አጋንንቶች በመንፈሳዊ ሰዎች አድማስ ውስጥ የሚሠሩት እዚህ ላይ ነው።

79 አሁን እዚህ ውስጥ ጥልቅ የሆነ ነገር አለና፡ በጣም ጥልቅ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን 1ኛ ሳሙኤል 28 ላይ፡ እዚህጋ አሁን የተወሰኑ ጥቅሶችን ማንበብ እፈልጋለሁ። በጥሞና እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ። እኔም ስለ "አጋንንት"፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ በትክክል እንዴት እንደሚሰሩ፡ ሰይጣን በእያንዳንዱ እውነተኛ ነገር ላይ የማስመሰል ውሸት እንዳለው መናገር እፈልጋለው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡ አጋንንት በክርስቲያኖች መካከል እንደሚመጡ እና ክርስቲያኖችን እንደሚመስሉ፡ አሁን ማየት ትችላላችሁ።

80 ብዙ ጊዜ ሰዎች "በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ" ሲሉን፡ ክርስቲያኖች መሆናቸውን እናውቃለን። ለምን፡ ዲያብሎሶችም ያምናሉ፡ ይንቀጠቀጡማል። ይህ ግን የመዳናችሁ ምልክት አይደለም። ከእነዚህ ምሽቶች በአንዱ ስለመመረጥ እናገራለሁ፡ ያን ጊዜ መዳን ምን ማለት እንደሆነ ታያላችሁ። እያችሁ? ከፊተኛውም ቢሆን፡ በኋለኛው፡ እናንተን የሚመለከት አይደለም፡ ወይም እናንተ የምትጨምሩት ነገር የለም። እግዚአብሄር ሰውን፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አድኗልና። ወዳጄ፡ ዘልቆ ይገባል፡ አይደል? አሁን፡ ከዚህ ሳንወጣ፡ ይህን ከስርዓታችሁ ውስጥ ማስወጣት አለብን። በጣም ጥሩ።

81 አብርሃም የእምነታችን ጀማሪ ነበር። ልክ ነው? ኦህ፡ አብርሃም ተስፋውን ያዘ። እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው ታላቅ ሰው ስለነበረ፡ ነውን? አይደለም፡ ወዳጄ! ከባቢሎን ወርዶ፡ በከለዳውያን ምድር፡ በ—በኡር

ከተማ እግዚአብሔር ጠርቶት፡ ቃል ኪዳኑንም ያደረገለት፡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነው። "እድንሃለው። አብርሃም ሆይ፡ አንተን ብቻ ሳይሆን፡ ዘርህንም እድናለው፡" ያለምንም ቅድመ ሁኔታ።

82 እግዚአብሔር ከሰው ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋል፡ ሰው ግን ቃል ኪዳኑን ሁልጊዜ ያፈርሳል፣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ፈጽሞ አይጠብቅም (ሕጉን አልተበቁትም፣ ሕጉን መጠበቅ አልቻሉም፣ ክርስቶስ ራሱ መጥቶ፡ ሕጉን ሰበረው።) ጸጋ አስቀድሞ አዳኝ አዘጋጅቶ ነበርና፡ ሙሴ፡ የማምለጫ መንገድ፡ አዘጋጅቶ ነበር፡ ማለቴ ማምለጫ አዘጋጀ፡ ከዚያ ህዝቡ፡ ከዚያ በኋላ፡ አሁንም የሆነ ነገር ማድረግ ፈለጉ። የማይቻላችሁ ነገር ሆኖ ሳለ፡ ሰው ግን ሁልጊዜ እራሱን ለማዳን አንድ ነገር ለማድረግ ይሞክራል። ይህ ተፈጥሮው ነው። እርቃኑን እንደሆ እንዳወቀ፡ በኤደን የአትክልት ስፍራ ውስጥ፡ ወድያው የበለስ ቅጠል ልብስ ሠራ። ልክ ነው? በኋላ ግን እንደማይጠቅም ተረዳ። ሰው በሰራው ነገር እራሳችሁን ማዳን አትችሉም። ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ፡ በዘመናት ሁሉ፡ እግዚአብሔር ያድናችኋል። ከዚያም ከዳናችሁ፡ ድናችኋል።

83 አብርሃምን ተመልከቱ። ያ ሰው፡ ሄደ፡ እግዚአብሔርም የፍልሰጤምን ምድር ሰጠውና ከዚያ እንዳይወጣ ነገረው። ፍልሰጤምን ለቆ የሚወጣ አይሁዳዊ ሁሉ ከእምነት ቀርቷል። እግዚአብሔር በዚያ ሁን ብሎታልና። እግዚአብሔር ሌላ ነገር እንድታደርጉ ቢነግራችሁና፡ ባታደርጉት፡ ከእምነት ወደ ኋላ ቀርታችኋል። ልክ ነው? መልካም፡ የአብርሃም እምነት እንዲፈተን፡ ድርቅ ተከሰተ። አብርሃምም እዚያ ከመቆየት ይልቅ፡ አልጸናምና፡ እዚያ መቄየት አልቻለም፡ ሸሽቶ ሄደ፡ ሣራን ይዞ ወደ ሌላ ምድር ወደ ሦስት መቶ ማይል ያህል ተጓዘ (በዚህ ላይ ለመናገር ጊዜ ቢኖረኝ ደስ ባለኝ።)

84 ወደዚያ ሲወርድ፡ ወደዚያም ሲወርድ ታላቁን ንጉሥ፡ አቤሜሌክን ተገናኘው። አቤሜሌክም ወጣት ነበርና ፍቅረኛ ፍለጋ ላይ ነበር፡ ስለዚህ የአብርሃምን ሚስት፡ ሣራን አገኛትና፡ ከእሷ ጋር ፍቅር ያዘው። አብርሃምም "አሁን፡ እኅቴ እንደሆንሽና እኔ ደግሞ ወንድምሽ እንደሆንኩ ንገሪው፡" አላት።

85 ይህም አቢሜሌክን ደስ አሰኘው፡ ስለዚህም እርሱ "በጣም ጥሩ፡ ወደ ቤተመንግሥት እንወስዳታለን፡" አላቸው። ሴቶች ሁሉ አሰማምረዋታል ብዬ እገምታለሁ፡ በነጋታው ሊያገባት ተዘጋጅቷል።

86 አቢሜሌክም ጥሩ፡ ጻድቅም ሰው ነበር። በዚያ ሌሊት፡ ተኝቶ ሳለ፡ ጌታ ተገለጠለትና "አንተ ሙት ሰው ነህ፡" አለው። "ልታገባት… የወሰድካትት ሴት፡ የሌላ ሰው ሚስት ናት፡" አለው። አሁን ተመልከቱ። "የሌላ ሰው ሚስት።"

87 እና፡ እርሱም "ጌታ ሆይ፡ የልቤን ቅንነት አንተ ታውቃለህ፡" አለው፡ ጻድቅና፡ ቅዱስ ሰው ነበርና። "የልቤን ቅንነት ታውቃለህ። ሰውዬው ራሱ 'እኅቴ' ናት ብሎኛልና። እርሷስ ይህ 'ወንድሜ' ነው፡ ብላ ራሷ፡ አልነገረችኝምን? "

88 እርሱም፡ እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፡ "የልብህን ቅንነት አውቄአለሁ፡ ስለዚህም በፊቴ እንዳትበድል ከለከልኩህ። እሱ ግን የራሴ ነብይ ነው!" ሃሌሉያ!

89 በምን ሁኔታ ነበር? ከእምነት ወደኋላ ወድቆ፡ በሰሱም፡ ውሸት ቢጤ ነካክቷል። ልክ ነው? ኧረ፡ የለም፡ የውሸት ትንሽ የለውም። ወይም ጥቁር

ውሸት ወይም አለመዋሸት ብቻ ነው። ሰውዬው ሚስቱ ስትሆን በዚያ ተቀምጦ ውሸቱን፡ “እህቴ” ነች በማለት ድብን-አርጎ ዋሸ፡ ዳር ዳር እያለ፡ ከእምነት ወደቀ።

90 እነሆም ጻድቅ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ፡ እንዲህ አለ፡ “ጌታ ሆይ፡ አንተ ልቤን ታውቃለህ።”

91 “አቤሜሌክ ሆይ፡ ጸሎትህን ግን አልሰማም፡ እርሷንም መልሰ... መልሣትና እርሱም ይጸልይልህ። እርሱ የራሴ ነብይ ነው፣ እርሱንም እሰማዋለሁ።” አዎን፡ ከእምነት የወደቀ፡ ውሸታም፡ ቢሆንም፡ “የግሌ ነብይ ነው።” እውነት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ነው።

92 ስለዚህ፡ በካልቪኒስቶች ትምህርት “አንዴ ጸጋ፡ ሁል ጊዜ ጸጋ ነው” በማለት፡ እካኪ ዘራፍ አትበሉ፡ ምክንያቱም ውርደት ውስጥ ትገባላችሁ። አያችሁ? አሁን፡ አንድ አፍታ፡ በዚህ ሳምንት ይህንን ለማንሣት እና ምን ያህል ደረጃውን የጠበቀ እንደሆነ ለማሳየት ጊዜ እናገኛለን። ይሁን እንጂ አንድ ስሕተት ስለሠራህ ለዘላለም እጠፋለሁ ብለህ አታስብ። የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፡ ከእግዚ አብሔር መንፈስ ተወልዳችኋልና፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናችሁ፡ ፍሬዎቹም ስለራሳቸው ይመሰክራሉ። ይኸው።

93 አሁን፡ እነሆ እዚህ ምድር ላይ፡ ተቀምጠናል። አሁን፡ 6ኛውን ቁጥር፡ ማንበብ እፈልጋለሁ።

> **ሳኦልም እግዚአብሔርን ጠየቀ፡ እግዚአብሔርም በሕልም፡** ወይም **በኡሪም፡** ወይም **በነቢያት፡** አልመለሰለትም።
>
> ሳኦልም **ባሪያዎቹን፡ ወደ እርሰዋ ሄጄ እጠይቅ** ዘንድ፡ **መናፍስትን የምትጠራ ሴት፡ ፈልጉልኝ አላቸው።**

እዚህ ላይ አንድ ነገር መዘርዘር እችላለሁ፡ መ... “መናፍስትን የምትጠራ ሴት ፈልጉልኝ።”

> **... ባሪያዎቹም፡** እነሆ፡ **መናፍስትን** የምትጠራ **አንዲት** ሴት **በዓይን-ዶር** አለች **አሉት።**
>
> **ሳኦልም መልኩን ለውጦ፡ ሌላ ልብሰም፡** ለብሶ **ሄደ፡** ሁለትም... **ሰዎች፡ ከእርሱ ጋር ነበሩ፡ በሌሊትም ወደ ሴቲቱ መጡ፥ እርሱም፡** እባክሽ፡ **በመናፍስት፡... -**አምዋርቺልኝ፡ የ... **የምልሽንም አስነሽልኝ አላት።**
>
> **ሴቲቱም እነሆ፡ መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን** ከምድር **እንዳጠፋ፡ ሳኦል** ያደረገውን **ታውቃለህ፡** ያውቃል፡ **መናፍስት የሚያውቁትን** ሁሉ፡ **አብርሯል፡ እና... ጠንቋዮችንም ከምድር ወጡ፡** ስለ ምን... **እኔን ለማስገደል** ወጥመድ **ለነፍሴ ታደርጋለህ፡ አለችው?**
>
> **ሳኦልም**፡ ሕያው፡ **እግዚአብሔርን፡ በዚህ ነገር፡** ቅጣት **አያገኝሽም** ብሎ **በእግዚአብሔር ማለላት...**
>
> **ሴቲቱም ማንን... ላስነሣልህ? አለች፡ እርሱም፡ ሳሙኤልን አስነሽልኝ አለ።**

**ሴቲቱም ሳሙኤልን ባየች ጊዜ፡ በታላቅ ድምፅ ጮኸች፡ ሴቲቱም፡ ሳኦልን፡ ለምን አታለልከኝ? አንተ ሳኦል ነህና።**

**ንጉሡም፡ አትፍሪ፡ ያየሽው ምንድር ነው አላት? ሴቲቱም ሳኦልን፡ አማልክት ከ... ከምድር ሲወጡ አየሁ አለችው።**

**እርሱም፡ መልኩ** ምን **ዓይነት ነው? አላት እርሰዋም፡ ሽማግሌ ሰው ወጣ፤ መጐናጸፊያም ተጐናጽፎአል አለች። እና** ሳም-... (በእርግጥ፡ ያ የነቢዩ መጎናጸፊያ ነው። አያችሁ? )... **ሳሙኤል እንደ ሆነ ተረዳ፡ በፊቱም ተጐነበሰ በ... በምድርም ላይ፡** እጅ **ነሣ።**

**ሳሙኤልም ሳኦልን፡** ለምን **አወክኸኝ፡** ለምንስ **አስነሣኸኝ አለው? ሳኦልም መልሶ፡** እንዲህ አለ፡ **እጅግ ተጨንቄአለሁ፡ ፍልስጥኤማውያን ይወጉኛልና፡ እግዚአብሔርም ከእኔ ርቆአል፡** አይመልስል**ኝምም**፡ **በነቢያት** ወይም፡ **በ**ሕልም አልመለሰልኝም፡ **ስለዚህም የ... የማደርገውን ታስታውቀኝ** ዘንድ፡ **ጠራሁህ አለው።**

እና **ሳሙኤልም አለ፡ እንደዛ ከሆነ... ለምን ት... ትጠይቀኛለ፡ እግዚአብሔር** ከራቀህ፡ **ጠላትም ከ—ከሆነህ ለምን ትጠይቀኛለህ?**

**እግዚአብሔርም** በቃሌ **እንደ** ተናገረ፡ **አድርጎአል፡ እግዚአብሔርም፡ መንግሥትህን** ከእጅህ ነጥቆ **ለ... ለጎረቤትህ ለዳዊት ሰጥቶታል፥**

94 አሁን፡ ብዙዎቻችሁ፡ ይህን ታውቃላችሁ። አሁን በቀጥታ በዚህ ላይ እንነጋገራለን፡ አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች፡ በዚህ ላይ ለመነጋገር፡ እግዚአብሔር ይርዳን። አሁን ተመልከቱ። ሳኦል፡ የተባለ ሰው፡ በአንድ ወቅት ሳኦል ከነቢያት ጋር ትንቢት ይናገር ስለነበር፡ ነቢይ ተደርጐ ይቈጠር ነበር። ልክ ነው፡ አስተማሪዎች? አሁን፡ ይህ ሰው ከእምነት ወድቆ ነበር። ልክ ነው? ሳሙኤል ግን፡ በሚቀጥለው ቀን ከእሱ ጋር እንደሚሆን፡ የተናገረውን አስታውሱ። ያለጊዜው ሄደዋል፡ አያችሁ። መልካም፡ እግዚአብሔርን ካላከበራችሁ፡ እግዚአብሔር ከምድር ይወስዳችኋል።

95 ጳውሎስ እነዚያን ሰዎች እንዴት እንዳደራጃቸው፡ በቆሮንጦስ ደብዳቤው ላይ ተመልከቱ። እንዲህ አላቸው፡ "በመጀመሪያ፡ እንዲህ ያለ ነገር በመካከላችሁ ስለሌለ፡ ስለእናንተ፡ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡ የ—የመንፈሳዊ ስጦታ እንዳይጎድልባችሁ።" በማለት በክርስቶስ ላይ፡ ምን አይነት ቦታ፡ እንዳላቸው ይናገራል። ከዚያም ስለ ሴት ሰባኪዎቻቸው፡ እንዴት እንደነበሩ፡ በጌታ ማዕድ ላይ እንዴት እንደሚበሉ፡ በመናገር በላያቸው ላይ መዶሻውን ማውረድ ጀመረ።

እንዲያውም አንድ ሰው ከእንጀራ እናቱ ጋር አብሮ የሚኖር ሲሆን፡ እርሱም ለዚያ ሰው በክርስቶስ፡ "ለሥጋው ጥፋት ለዲያብሎስ፡ አሳልፌ ሰጠሁት፡ ነፍሱ ትድን ዘንድ" አለ። አያችሁ፡ ያ ነው፡ አሳልፌ ሰጠሁት። መጽሐፍ ቅዱስም ይላል፡ "ስለዚህም በእናንተ ዘንድ ብዙ ደካማዎችና ሕመምተኞች አሉ፡ ብዙዎችም አንቀላፍተዋል፡" በኃጢአት ምክንያት ያለጊዜ መሞት።

እግዚአብሔር ከመንገድ ካወጣችሁ፡ ክርስቲያን እንደሆናችሁ፡ ጥሩ ምልክት ነው።

96 ስለዚህ፡ እዚህ ጋር ልብ በሉ፡ ሳኦል ከነቢያት አንዱ ተደርጐ፡ ወይም ከነቢያት መካከል አንዱ ተደርጐ ይቈጠር ነበር፡ ምክንያቱም ትንቢት ተናግሯል። እግዚአብሔርንም ባለመታዘዙ፡ አሁን ከእምነት ወድቋል፡ መንግሥቱም ከእጁ ተቀዶ እግዚአብሔርም በሳሙኤል ዘይት፡ በቀባው፡ በዳዊት እጅ ተላልፎ ተሰጠ።

97 ስለዚህ፡ ከእግዚአብሔር የሚመጡትን ነገሮች ለማወቅ ሦስት መንገዶች እንደነበሩ፡ ልብ በሉ፥ የ—የመጀመሪያው ነቢይ፡ ሁለተኛው ሕልም፡ ሦስተኛው ደግሞ ኡሪምና ቱሚም ነበር። አንዳቸውም ለሳኦል ምንም መልስ አልሰጡም። እንግዲህ፡ ነቢይ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ መንፈሳዊ ሕልም ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ኡሪምና ቱሚም ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ። ይኸውላችሁ፡ በቀደም አ—አንድ ሰው ስለ ኡሪም ጠየቅሁት፡ ያ ሰው ኡሪምና ቱሚም ምን እንደሆነ፡ ሊነግረኝ አልቻለም። እርግጥ ነው፡ በእነዚያ አማካኝነት መልስ ሲሰጥ የነበረው እግዚአብሔር ራሱ ነበር። አያችሁ?

98 ሰይጣንም በእነዚያ ሁሉ ቅጥፈትን ያደርጋል፥ ጠንቋዩ፡ ሐሰተኛው ነቢይ፡ ክሪስታል መስታወት። አያችሁ?

አሁን፡ የቱሚም ኡሪም በአሮን ደረት ላይ **እዚህጋ**፡ ይንጠለጠላል፡ ቱሚምና ኡሪም በዕንቆች ይሸፈናል። ከዚያም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይሰቅሉታል። ጥርጣሬ ሲገባባቸው፡ መልስ ለማግኘት፡ ወደ እግዚአብሔር ፊት ይሄዳሉ፡ ብርሃንም በኡሪምና ቱሚም ላይ ይበራል፡ ይህም፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነና፡ እንዳልሆነ ለማወቅ ነው። አሁን፡ የኡሪምና ቱሚም መልስ ካልሰጠ... ያ ማለት፡ ቀጥተኛ የእግዚአብሔር መልስ ነው።

አሁን፡ የዛሬው ኡሪምና ቱሚም፥ ጠንቋይ የሐሰትን ነገር ለመዘባረቅ፡ እንደ ተምሣሌት፥ የክሪስታል ኳስ ይይዛል። እግዚአብሔር በሰላሴ ውስጥ፡ የእግዚአብሔር ኃይል በሰላሴ ውስጥ ነው። ዲያብሎስም ስላሴ ውስጥ ነው፡ ኃይሉም በሰላሴ ውስጥ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጥ እችላለሁ። እና ያ ኡሪም እና ቱሚም፡ ዲያብሎስ ዛሬ የ... የክሪስታል ኳስ አድርጎ ይጠቀማል። ዛሬም የሐሰተኛው ነቢይ፡ አሁን ያለው ሰው፡ የነበረን፡ ወይም፡ ይህ፡ ወይም እዚያ ያለው ጠንቋዩ፡ የነቢዩን ሰፍራ ለመተካት፡ ከዲያብሎስ ጐን ቆሟል። ምን ማለቴ እንደሆነ ታያላችሁ?

99 ስለዚህ፡ አሁን፡ በአሁኑ ዘመን ኡሪምና ቱሚም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው። አንድ ሰው ትንቢት ወይም ሕልም ቢናገር፡ ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ካልተመሳሰለ ወይም ካላስተጋባ፡ ሐሰተኛ ነው። አትመኑት።

100 በቅርብ ጊዜ፡ አሁን ለመሄድ እየተዘጋጀሁበት ካለው፡ ከህንድ አገር፡ አንድ ምስኪን ሰባኪ ወደ እኔ መጣና። "ወንድም ብራንሃም፡ ወደዚህ መጥቻለሁ፡" አለኝ። "መንፈስ ቅዱስ የተሞላች ሴት ናት፡ እና፡" አለኝ፡ "በጣም መልካም፡ ጥሩ ሴት ነች፡" አለኝ። እንዲህ አለ፡ "አራት ጊዜ አግብታለች፡ አሁንም ከአራተኛው ባሏ ጋር ትኖር ነበር። እኔም፡ 'እንዴ፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል፡ ጌታ ሆይ' አልኩኝ? " እንዲህም አለ፡ "በእርሱ ፊት ቀርቤ እንዲህ አልኩ፡ 'ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!' 'ሃሌ ሉያ! ጌታ ይመስገን' አልኩኝ

አለ!" ልክ እንደዚያ ዓይነት፡ ታውቃላችሁ። "ሃሌ ሉያ! ጌታ ይመስገን!' አለ፡" "ጌታም እንዲህ ብሎኛል፡ 'እነሆ፡ ሕልም አሳይሃለሁ' ብሎኛል፡" አለ። ከዚያም እንዲህም አለ፡ "እነሆ ሕልም አለምሁ፡ ባለቤቴም ስታመነዝር አየሁ። ወደ እኔም ተመልሳ፡ 'ኦህ፡ ቪክቶር፡ ይቅር ትለኛለህን? ይቅር ትለኛለህን? እና... ' 'ታዲያስ፡' 'አዎን፡ ይቅር እልሻለው እንደገና ወደ እኔ እመልስሻለሁ፡' አልኳት።" "እና፡ እኔ ያደረኩት ያንን ነው፡" አለኝ። "አየህ፡ ይቅር እልኳት፡" አለ።

101 እኔም "ቪክቶር፡ ሕልምህ በጣም ደስ ይላል፡ ያሳየህ ግን ዲያብሎስ ነው፡" አልኩት።

"ለምን፡" አለኝ?

102 እኔም፡ "ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አታነጻጽረው። በምንዝርና እየኖረች ነው። ያለጥርጥር። ከአራት ወንዶች ጋር መኖር አትችልም። በትክክል። ያንን ትታ ወደ መጀመሪያው ከተመለሰች፡ ከፊት ይልቅ የከፋች ናት። ቀሪ ሕይወቷን በሙሉ፡ ሳታገባ መኖር አለባት" አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ "ይህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሊወዳደር እንደማይችል ታውቃለህ። ስለዚህ... ህልምህ ውሸት ነበር።" "ከዚህ ጋር አይነጻጸርም፡" አልኩት።

103 ነቢይ ትንቢት ቢናገር፡ በተናገረ ጊዜ፡ ትንቢቱ እውነት መሆን አለመሆኑን ለማወቅ፡ በኡሪምና ቱሚም ፊት ያቀርቡት ነበር። የእግዚአብሔርም ድምፅ በኡሪም ቱሚም ላይ ብርሃን ካበራ፡ ከዚያ ትንቢቱ ፈጽሞ፡ እውነት ነው። እና ሰው ቢተረጉም፡ ወይም ሕልሙን ቢነግር፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የሆነ ነገር፡ ወይም ሌላ ነገር ቢናገር፡ ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ካልተመሣሰለ፡ ሐሰተኛ ነው። ዛሬም ኡሪም ቱሚም አለ። መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት እንደነበረው ኡሪም ቱሚም፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ድምጽ ይነገር ነበር። አሜን! ሃሌሉያ! እመነት እምነት ተሰማኝ። እንደ እክራሪ የምታዩኝ ካላችሁ፡ እንደዛ አትውሰዱኝ። ያለሁበትን አውቀዋለሁ፡ አውቃለሁ። አልደነቀኝም። በትክክል።

104 እውነት ይህ ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል! ምን ዓይነት ሕልምም ብታልሙ፡ ወይም ምን ዓይነት ትንቢት ብትናገሩም ግድ አይሰጠኝም፡ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከሌለ፡ ከቃሉ ጋር ካልተሰማማ፡ ስሕተት ነው። በዛሬው ጊዜ ያለው ችግር ይህ ነው። ለአንዱ ሕልም አለው፡ ለአንዱ ራእይ አለው፡ አንዱ ልሳን አለው፡ አንዱ ራእይ አለው፣ ሁሉም ነገር እና በአጠቃላይ በጣም ግራ ተጋብቷል፡ የሃይማኖት ተቋም መሰረታችሁ እነሆ ሁሉንም ነገር አፈረሳችሁ። ወደ ፍጻሜው መሠረት መመለስ አለባችሁ፡ ያም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በትክክል።

105 ብዙ አብያተ ክርስቲያንት እየተገነቡ ያሉት፡ አንዱ "ኦህ፡ ኢየሱስ በነጭ ፈረስ ላይ እየመጣ ነው። አውቃለሁ፡ በራእይ አይቼዋለሁ፡" ብሎ በተናገረው ነው። እንደዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ይሠራሉ። "ኦህ፡ ሃሌሉያ! በደመና ላይ እየመጣ ነው።" በእንደዚህ ዓይነት መሰረት ላይ ይሠራሉ። ከዚያም ያንን አፍርሰው፡ ይለያዩና፡ እርስ በርሳቸው፡ "የጥምባንሳ ሰብሰብ፡" እና "የቅማል ማረፊያ" እና የመሳሰሉትን ነገር በማለት ይጠራራሉ። ለምን፡ ወንድሜ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ እንዲህ ስታደርግ ልብህ በእግዚአብሔር ፊት፡ ትክክል

እንዳልሆነ ያሳያል። በትክክል። ወንድማማቾች ነን። አንዳችን ከሌላው ጐን መቆም አለብን። አንዳችን ለሌላው እናስፈልጋለን።

106 አሁን ተመልከቱ። ሳኦል ባክ አደረገና፡ ወደ አንድ ሰፍራ ወጣ። እርሱ፡ ማለት እግዚአብሔር፡ ፊቱን ከሳኦል ላይ አዞረ። ወጣና ነብያቶችን ጠየቀ። ነቢያትም ለመተንበይ ሞከሩ፡ እግዚአብሔርም ዝም አላቸው፡ እንዳይተነብዩ ራእይም ከለከላቸው። ነቢዩ መጣና፡ እንዲህ አለ፡ "አልችልም። አይ። እርሱ ስለአንተ ምንም አልነገረኝም" አለው።

107 መልካም፡ ከዚያም እርሱ "ጌታ ሆይ፡ በሕልም ተናገረኝ፡" አለ። ከሌሊት ወደ ሌሊት፡ ምንም ህልም የለም።

108 ከዚያም ወደ ኡሪም ቱሚም ገብቶ፡ እንዲህ አለ፡ "እግዚአብሔር ሆይ! ነቢያትን ሞክሬያለሁ፡ ህልሞችን ሞክሬያለሁ፡ አሁን እርዳኝ። እሺ ትለኛለህን? " ምንም ብርሃን አልበራም፡ ዝም አለው።

109 ከዚያም ወደ ተዋረደች፡ ዝቅተኛ፡ ጠንቋይ ጋር ወረደ። ወደ እርሷ ሄዶ፡ ራሱን ለወጠና ወደ ውስጥ ዘልቆ ገባ። ይህች ጠንቋይ ወጥታ የሳሙኤልን መንፈስ ጠራች።

110 አሁን፡ ምን እያሰባችሁ እንደሆነ አውቃለሁ። ብዙዎች "ያ ሰው ሳሙኤል አይደለም፡" ይላሉና። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ሳሙኤል እንደሆነ ይናገራል። ይህንን ለመረዳት እንግዳ ነገር ነው፡ አይደል? ነገር ግን ያ ሳሙኤል ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ ነው ይላል።

111 እና ጠንቋይዋ እርሱን መጥራት ተችሏታል፡ ሳሙኤልንም ጠራችው። ሳሙኤልም ሌላ ቦታ ነበር፡ ይሁን እንጂ ምን እየተካሄደ ስላለው ነገር ግን ህሊናው ያውቅ ነበር፡ አሁንም የነቢይ መጎናጸፊያ ለብሶ ቆመ። ስለዚህ፡ ወንድሜ፡ ሰትሞት፡ በሆነ ቦታ ላይ ኖሮ እየኖርክ፡ ሌላ ቦታ እየኖርክ ነው እንጂ፡ አልሞትክም።

112 ስለ አጋንንት በትንሹ ለመረዳት፡ ለትንሽ ደቅቃ ቆም ልበል። እርሷ አጋንንት ነበረች፡ ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር ግን የጠበቀ ግንኙነት ነበራት። አሁን፡ ዛሬ፡ ራሳቸውን ክርስቲያን አድርገው ከሚያምኑ ሰዎች ይልቅ ስለመንፈሳዊው ዓለም የበለጠ የሚያውቁ ብዙ መንፈሳዊያን አሉ፡ ነገር ግን አጋንንት ነች። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበረው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው።

113 ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ ፕሮፌሰሮች ምሁራን እና አስተማሪዎች ነበሩ፡ አንዳንዶቹም በዛሬው ጊዜ ካለን ፡ የተሻለ ከሥነ መለኮት ትምህርት ቤት የመጡ ናቸው። እና ቅዱስ፡ ታዋቂ ሰው፡ እነሱ መሆን ነበረባቸው። አንዱ ሌዋዊ ከተባለ፡ በሁሉም መንገድ እንከን የለሽና፡ ጻድቅ ሆኖ መታየት ይኖርበታል። ሰውየው ሰለ እግዚአብሔር የሚያውቀው ነገር ቢኖር ግን ጥንቸል ሰለ በረዶ ጫማ ከምታውቀው ያህል የዘለለ አልነበረም። ኢየሱስ ሲመጣ፡ አላወቀውምና፡ ኢየሱስን "ዲያብሎስ" ብሎ ጠራው። እንዲህ አለ፡ "የዲያብሎስ አለቃ የሆነው፡ ቡኤልዜቡል ነው" አለው። ልክ ነው?

114 በመቀጠል የምናገኘው ዝቅተኛው አይነት አጋንንት፡ በመቃብር ሰፍራ ያንን ሰው አሰሮ የነበረ፡ እና ውዘተረፈ ነው፡ እነርሱም ጮኹ። ዲያብሎስ ራሱ እንዲህ አለ፡ "ማን እንደሆንክ እናውቃለን። አንተ ቅዱሱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ"

አሉ። ልክ ነው? ጠንቋዮችና አስማተኞች፡ አጋንንቶች፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አወቁት፣ የተማሩ፡ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ሰባኪዎች ግን እርሱ ቡኤልዜቡል ነው አሉ። ማን ትክክል ነበር፡ ዲያብሎስ ወይስ ሰባኪው? ዲያብሎስ ትክክል ነበር። እናም፡ ወንድሜ ሆይ፡ ዛሬም ያው ነው አልተለወጠም። የእግዚአብሔርን ኃይል አያውቁትም።

115 ምንም ያህል ትምህርት ቢኖራችሁም፡ ምንም ያህል ወደ ውስጣችሁ ብትጎስሙትም። እግዚአብሔር በትልልቅ ቃላት ውስጥ አይገኝም። እግዚአብሔር በቅን ልብ ውስጥ ነው። እዚህ ላይ ቆማችሁ፡ እኔ የማላውቀውን፡ ትልልቅ ቃላትን መናገር ትችላላችሁ፡ ያ ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርባችሁም። ቆማችሁ ሰብከታችሁን እንዴት መድገም እና መናገር እንዳለባችሁ ልትለማመዱ ትችላላችሁ፡ ያ ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርባችሁም። ይዛችሁት እስክትተኙ ድረስ ዲክሽነሪ ልታጠኑ ትችላለህ፡ ይህም ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርባችሁም። ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርባችሁ፡ ትሑት፡ ራሱን የሚያስገዛ፡ ቀለል ያለ ልብ ነው። ይህም እውነት ነው። አሜን! ትሑት ልብን፡ እግዚአብሔር ይወዳል። አሁን፡ ሀሁን አለማወቃችሁ፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። ትሑት ልብ ብቻ ይኑራችሁ! እግዚአብሔር በትሑት ልብ ውስጥ ያድራልና፣ በትምህርት አይደለም፡ በትምህርት ቤቶችም አይደለም፡ በሥነ መለኮት አይደለም፡ በሴሚናሪዎች አይደለም፡ በሌሎች ልዩልዩ ቦታዎችም አይደለም፣ በትላልቅ ቃላት አይደለም፡ ወይም በቅንጡ ቦታዎች አይደለም። እግዚአብሔር ግን በሰው ልብ ያድራል። ራሳችሁን ዝቅ ባደረጋችሁ መጠን፡ ይበልጥ ትሑት ትሆናላችሁ፡ በእግዚአብሔር ዓይን ግን ታላቅ ትሆናላችሁ።

116 እስኪ ይህን ነገር ልስጣችሁ። እርሻዎቻችሁ ሰንዴን አዝለው አይቻቸዋለሁ። ጭንቅላት ላይ የተሞላ ሰንዴ ሁል ጊዜ ያጎነብሳል። በመካከላቸው ብቅ ብሎ የወጣ ቅጠል አይቻለሁ፡ እና ሁሉንም እንደሚያውቅ እንዲህ ይወዛወዛል፡ ጭንቅላቱ ላይ ምንም ሰሌለው ነው። እነዚህ ሰዎችም ብዙዎቹ ኣንዲሁ ናቸው በአእምሮአቸው ውስጥ ብዙ ነገር እንዳላቸው ያስባሉ፡ ግን'ኮ፡ በልባቸው ውስጥ ምንም የላቸውም። ቅዱስ የሆነ ጭንቅላት ስለ ስልጣኑ ይሰግዳልና፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር ልጅ ይቀበላል፡ በሥራዎቹም ያምናል።

117 "እርሱም ትላንት፡ ዛሬም ያው ነው።" ኦህ፡ እርግጥ ነው፡ ከታሪክ አንጻር፡ ያውቁታል። እርሱ ግን ታሪክ አይደለም። ሰዎች ተነሥተው "ታላቅ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና የመሳሰሉት ነገሮች ሲኖሩ፡ ኦህ፡ በጴንጤቆስጤ እናምናለን፡" ይሉና፡ የእሳትን ሰዕል ይሰላሉ። የበረደው ሰው በተሳለው እሳት ሊሞቅ አይችልም። የተሳለ እሳት አያሞቅም። እነርሱም እንዲሁ ናቸው። እሱ ትናንት፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው ከሆነ ዛሬስ እንደት ነው? ያ የተሳለ እሳት ነው። አንድ አንድ ሰዎች በብርድ ሊሞቱ ደርሰው፡ "እነዚያ ያላቸውን ትልቅ እሳት ተመልከቱ፡" ይላሉ። እንዴት፡ ያ'ኮ እናንተን አያሞቃችሁም።

118 በጴንጤቆስጤ ዕለት ያደረጉትን፡ በአዲሱ ኪዳን የነበራቸውን፡ እኛ ዛሬ አለን! እግዚአብሔር ሁሉን ተኩሶ አስተካክሎ፡ ቤተ ክርስቲያኗን አንድ ላይ አቀናጅቶ ከጨረሰ በኋላ፡ መነጠቅ ይሆናል። ነገር ሁሉ ከመበላሸቱ የተነሣ ግን፡ ለንጥቀት ይቅርና፡ ለመለኮታዊ ፈውስ እንኳን እምነት የለንም፡ እንዱ **በዚህ**

እንዱ **በዚያ**። “ዶክተር **እከሌ-እና-እከሌ ይህ** ነው ብለዋል። እና፡ ሰባኪያችን ደግሞ **ይህ** ነው ብሏል።”

119 ቀደም ሲል፡ አንዲት ሴት፡ “እሱ’ኮ አጭበርባሪ ነው።” “ቄሳችን ነግሮኛል፡” ብላለች። ቄሷ አንድ ጊዜ ወደዚህ ቢመጣ ደስ ባለኝ፡ አጭበርባሪው ማን እንደሆነ እናይ ነበር። አዎን። አጭበርባሪ ማን እንደሆነ እናያለን። ና ሞክረው።

120 በቅርብ ጊዜ፡ በቴክሳስ፡ ሀርሊንገን ውስጥ፡ አንድ አገልግሎት ነበረን። በዚያም ምሽት ወደዚያ ስሄድ፡ በመኪኖቹ ላይ ትልልቅ ምልክቶች ነበሯቸው፡ እኔን እንደ አጭበርባሪ ለማጋለጥ ኤፍ ቢ አይ እዚያ እንደነበሩ ነገሩኝ። በቴክሳስ ውስጥ የሆነ ቦታ አንዲት ትንሽ ልጅ ተፈውሳ ነበር። የምትኖረው እጅግ ሩቅ፡ እና፡ ሰ—ገምት፡ አንድ ሺህ ማይል የሚያክል ርቃ፡ በፓንሃንድል አከባቢ ነች። ይህም በሃርሊንገን ውስጥ፡ በድንበሩ ላይ ነበር። ወንድም ባክስተር መጣና፡ “ወንድም ብራንሃም፡” አለኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “እንዲህ ያለ ውጥንቅጥ ከዚህ በፊት አይተህ አታውቅም፡ አራት ወይም አምስት ሺህ ያህል ሰዎች አሉ።” “ስለዚህ፡ ዛሬ ማታ አንተን ከመድረኩ ላይ ለመያዝ፡ እና ለማጋለጥ፡ ኤፍ ቢ አዮች ዙርያውን ሞልተውታል፡” አለኝ።

እኔም “መልካም፡ እንዲህ በመሆኑ ደስ ይለኛል፡” አልኩት።

121 አልኩት፡ “በቀደም ምሽት የተፈወሰችውን ልጅ ታውቃታለህ?

122 ወደ ቤቴ እየመጣሁ ነበር... ወደ ክፍሌ እየገባሁ ነበር። የሆነ የሚጮኽ ድምጽ ሰማሁና፡ ዞር ብዬ ተመለከትኩ። ምናልባት አንድ ሰው ጥቃት ደርሶበት ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ። አንዲት ሴት ልጅ ናት። ወደ ኋላ ተመለከትኩ። ወ... ወደ ኋላ ተመለስኩና፡ “ምን ሆነሽ ነው፡ እመቤት፡” አልኳት? ሁለት ልጃገረዶች ቆመው ነበሩ፡ አሥራ ሰባት፡ አሥራ ስምንት ዓመት ገደማ፡ እያንዳንዳቸው፡ ክንድ ለክንድ ተቃቅፈው፡ እያለቀሱ ነበር።

123 “ወንድም ብራንሃም!” አሉኝ፡ ያን ጊዜ እንደሚያውቁኝ አወቅኩ። እንዲህ አለች፡ “እኛ፡ እስከዚህ ደርሰ ያመጣኋት እኔ ነኝ።” “ወደ እብዶች ሆስፒታል ትግባ ተብላለች፡” አለችኝ። ይህች ልጅ በሉብቦክ፡ በቴክሳስ ስብሰባዬ ላይ ነበረች። “እሷን ወደዚህ ባመጣት አንተም ለእርሷ ብትጸልይላት፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውሳት አምናለሁ፡” አለች።

124 መልካም፡ “ምን ዓይነት እምነት ነው!” ብዬ አሰብኩ፡ እንዲህ አልኳት፡ “መልካም፡ አሁን፡ እህቴ፡ እስኪ ወዲህ አምጪአት... ” ከዚያም እንዲህ አልኳት፡ “ወደዚህ ስትመጡ በቢጫ ሮድስተር መኪና ነው፡ አይደል? ”

“አዎን!” አለች፡

“እናትሽ አካል ጉዳተኛ ነች፡” አልኳት።

“ትክክል ነው፡” አለች።

“የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን አባል ነሽ፡” አልኳት።

“ይህ በትክክል እውነት ነው፡” አለችኝ።

125 እንዲህ አልኳት፡ “በመንገድ ላይ ስትመጡ፡ ልትወድቁ ደርሳችሁ ነበር። አንቺና ይህች ልጅ ግማሹ ኮንክሪት ግማሹም አስፓልት በሆነበት ቦታ መታጠፍያውን ስትዞሩ፡ እየሳቃችሁ ነበር።”

እሷም “ወንድም ብራንሃም፡ ይህ እውነት ነው፡” አለችኝ!

እኔም “እንግዲያውስ፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡ ልጅቷ ተፈወሳለች ይላል፡” አልኳት።

126 በቀጣዩ ቀን ከተማዋን እያቀጣጠለች፡ እየዞረች፡ ስለእሱ ለሁሉም ሰው ተናገረች። እርግጥ ነው፡ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ትኑር ወይም አትኑር፡ እሷን በዚያ አካባቢ እያውቋትም። ከዚያም በዚያ ቀን... ወንድም ባክስተር እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡” “ልጆቹ ታች ሻንጣቸውን እያዘጋጁ ነው፡” አለኝ። ይህም እኔ የማውቀው እሱ የማያውቀው አንድ ነገር ነው። የገንዘብ አቅማችን ተመናምኖ ነበር። ስለዚህ ጉዳይ እንዲናገር ፈጽሜ አልፈቅድለትም። ነገር ግን ከእነዚህ ልጃገረዶች መካከል አንዷ ከ—ከዚያ በፊት በነበረው ምሽት ምጽዋት ዘጠኝ መቶ ዶላር አስቀምጣ ነበር፡ ገንዜቡን ከላይ አደረገችው። እሱ፡ አላወቀም፡ እስከ ዛሬም አላወቀም፡ እኔ ግን አውቀዋለሁ። አያችሁ? እና... እግዚአብሔር ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል ብሎኝ ነበርና።

127 ወንድም ባክስተር እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡” “ትንሽ የገንዘብ መዋጮ እንድጠይቅ ፍቀድልኝ፡” አለኝ። “ከእነዚህን ሰዎች የገንዘብ መዋጮ የጠየቁ አንዳንድ መለኮታዊ ፈዋሾችም እዚህ አሉ፡” አለኝ።

128 እኔም፡ “አይሆንም። አይ፡ ወዳጄ። ምንም አታድርድ። ወንድም ባክስተር፡ እንደዚህ ዓይነት የገንዘብ መዋጮ ለማግኘት ከሞከርክ፡ እኔና አንተ እንደ ወንድማማች ተጨባብጠን፡ እኔም ለብቻዬ የምሄደው ያን ጊዜ ነው፡ አልኩት።” አያችሁ? አልኩትም፡ “ይህንን አታድርግ።” እንዲህ አልኩት፡ “እግዚአብሔር በሺህ ኰረብቶች ላይ ያሉ ከብቶች ባለቤት ነው፡ ነገር ሁሉ የእርሱ ነው። የእሱ ንብረት ነኝ። እርሱ ይንከባከበኛል አልኩት።”

“እሺ፡” አለኝ።

129 በዚያው ምሽትም እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ተመልከት። ኧረ ሰዎች... ወደዚህ ተመልከቱ! እዚህ ሰም ባልተጻፈበት ፖስታ ውስጥ፡ በውስጡ ዘጠኝ መቶ ዶላር አለ። የሚያስፈልገን የገንዘብ ልክ አገኘን።”

እኔም “ወንድም ባክስተር፡” አልኩት።

እርሱም “ይቅርታ አድርግልኝ፡” አለኝ።

130 ከዚያም ያቺ ልጅ እንደሆነች አወቅኩ። ስለዚህ በ—በቀጣዩ ቀን፡ ወንድም ባክስተር እንዲህ አለኝ፦ “ወንድም ብራንሃም፡ እነዚያ ልጆች ልብሳቸውን እየሰበሰቡ፡ እና እያለቀሱ ነው።”

እኔም “ምንድነው ችግሩ፡” አልኩት?

“ወደ ታች ወርደህ ብታያቸው ይሻላል፡” አለኝ።

131 ወደሚገኙበት ክፍል ወረድኩ። እኔም፡ “በየትኛው ክፍል ውስጥ ነው ያሉት? ” አልኩትና ወደዚያ ወርጄ በሩን አንኳኳሁ። ሲያለቅሱም ሰማኋቸው። በሩን አንኳኳሁ፡ እናም ልጅቷ ወደ በሩ መጣች፡ እንዲህ አለች፡ “ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ በጣም አዝናለሁ።” “ይህን ሁሉ ችግር ያመጣሁብህ እኔ ነኝ፡” አለችኝ።

እኔም፡ “ችግር? የምን ችግር ነው እህቴ፡” አልኳት?

እሷም እንዲህ አለችኝ፡ "ኦህ፡ ኤፍ ቢ አይ እየተከታተሉህ ነው።"

እኔም "ኦህ፡ የእውነትሽ ነው? " አልኳት፡

132 እርሷም "አዎ።" አለች፡ "ዛሬ በከተማው ዙሪያ ብዙ መሰክሬያለሁ፡ እንዲሁም ይህን ያን አድርጌአለሁ መሰለኝ፡" አለችኝ።

እኔም "አይደለም፡" አልኳት።

133 እሷም "ወንድም ብራንሃም፡ ኤፍ ቢ አይ እዚያ አሉ፡ እዚያ ናቸው፡ ዛሬ ማታ ያጋልጡሃል፡" አለችኝ።

134 እንዲህ አልኳት፡ "ይሁን፡ ምንም አይነት ስሕተት እየሰራሁ ከሆነ፡ ልጋለጥ ያስፈልገኛል።" አየሽ? እኔም "አዎን። ወንጌልን በመስበክ መጋለጥ ካስፈለገን፡ መልካም፡ ይሁና፡" አልኳት። አያችሁ? እንዲህ አልኳት፡ "እ—እኔ—የምኖረው በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ የማይናገረውን... ይሄው፡ ይህ ጠበቃዬ ነው።" አያችሁ? እና፡ እንዲህ አልኳት...

እሷም፡ "ብቻ፡" እንዲህ አለች፡ "ብቻ እኔ ያደረግኩትን በማድረጌ አዝኛለሁ።"

"እህቴ፡ ምንም ነገር አላደረግሽም፡" አልኳት።

እሷም "ታዲያ፡ አንተ ወደዚያ ለመሄድ አትፈራም፡" ብላ ጠየቀችኝ?

"አልፈራም፡" አልኳት።

"ግን እኮ፡ ኤፍ ቢ አይ በዚያ አሉ፡" አለችኝ።

135 "ችግር የለም፡ ከዚህ በፊትም በስብሰባዬ ላይ መጥተው፡ ድነው ተመልሰዋል፡" አልኳት። ስለ፡ "ሚስተር አል ፋራር... "

136 ካፒቴን አል ፋራር፡ ብዙዎቻችሁ ታኮማ፡ ዋሽንግተን ውስጥ ጌታ ስለመቀበሉ ታውቃላችሁ፡ የዳነው፡ እዚያ ታች በተኩስ ልምምድ ማዕከል አከባቢ ነው። በስብሰባው ወጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ "ይህን ሰው ለሁለት ዓመት ያህል ተከታትያለሁ። እና ስለ ፋይናንስ ሰማሁና፡ በደንብ ተከታተልኩት፡ እና በሁሉም ቦታ ሄድኩ።" እንዲህም አለ፡ "እውነት ነው፡ ዛሬ ማታ የምትሰሙት አንድ ወግ አጥባቂን አይደለም፡ የምትሰሙት እውነትን ነው አላቸው።" "በፖሊስ ኃይል ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች መካከል አንዱ፡ ዶክተሬ ልጁን እንዲመለከተው እንዳደረግኩና ወደ ጸሎት መስመር እንዲገባ ላክሁት፡" አክሎም፡ "ስለ ልጁ የተነገረው ነገር አስቀድሞ እንደተባለው፡ ችግሩ ምን እንደነበረ በትክክል ተነገረው። እንደውም አለ፡ 'በሰምንት ቀናት ውስጥ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሳል፡'" ችግሩ የፖሊዮ በሽታ ነው። እንዲህም አለ፡ "በሰምንተኛው ቀን ሕፃኑ ወደ ትምህርት ቤት ተመለሰ።" በአሥር ሺህ ሰዎች ፊት፡ "ለሁለት ዓመታት ያህል ተከታትዬዋለሁ፡" አለ። ሁሉም ነገር አለ... በ—በመጽሐፋችሁ ውስጥ፡ የሲያትል ጉባኤው፡ ፎቶግራፍ ተቀምጧል። እንዲህ አለ፡ "የምትሰሙት የሃይማኖት አባባል እንዳልሆነ ሁላችሁም እንድታውቁ እፈልጋለው። እየሰማችሁት ያላችሁት እውነት ነው።" አለ ካፒቴን አል ፋራር። በሚቀጥለው ቀን ጌታን አስቀበልኩት፡ ወዲያውም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተቀበለ፡ በዚያ በትልቁ፡ የተኩስ ልምምድ ስፍራ ውስጥ።

"ምናልባት ይህ ሰውዬም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡" አልኳት።

ስለዚህ እንዲህ አለች፡ “ወደዚያ ለመሄድ ትፈራለህ? ”

137 እኔም፡ “ትፈራለህ? ለምን፡ በፍጹም አልፈራም። በፍጹም አልፈራም አልኳት። እግዚአብሔር ይህን እንድሠራ ከላከኝ ለምን እፈራለሁ? ውጊያውን የሚዋጋው፡ እሱ እንጂ እኔ አይደለሁም።” ስለዚህም እንዲህ አልኳቸው፡ “አሁን፡ ሁላችሁም ከዚህ ነገር ውጡ።” ስለዚህ...

138 በዚያ ምሽት ወደ ሰብሰባ ሄድን፡ ሰፍራው በሰዎች ተሞልቶ ነበር። እና በዚያ የነበረው ተቆጣጣሪ ወጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ሬቨረንድ ብራንሃም፡ አሥር የሜክሲኮ ተወላጆች ቀጥሬብሃለሁ።” እንዲህ አለ፡ “እዚህ ላይ ተመልከቱ፡ ‘አክራሪው ሃይማኖተኛ፡ ሬቨረንድ ብራንሃም ዛሬ ማታ በኤፍ ቢ አይ ይጋለጣል፡’” ሌላም እንደዚህ ያለ ነገር ተናገረ። እንዲህም አለ፡ “በእያንዳንዱ መኪኖች ላይ አለ። እናጥፋው... ” “አሥር የሜክሲኮ ተወላጆች ቀጥሬአለሁ፡ ሁሉንም በመኪና ላይ ያሉትን አውጥተው ወደዚህ ያመጡአቸዋል፡” አለ። “ኦህ፡ ያን ሰው በያዝኩት ደስ ባለኝ፡” አለ!

139 እኔም፡ “አትጨነቅ፡ ወዳጄ። እግዚአብሔር ይይዘዋል” አልኩት። አያችሁ? “ብቻ ዝም በለው፡” አልኩት።

140 ስለዚህ መጣ። በዚያም ምሽት ሰንመጣ፡ መቼም አልረሳውም፡ ወደ ህንጻው ገባን። ወ... ወንድም ባክስተር **እመን ብቻ** ዘመረ። እንዲህ አለ፡ “አሁን፡ ወንድም ብራንሃም ዛሬ ማታ ሕንፃውን ለቅቀን እንድንወጣ ተናገረ።” “ወደ ኋላ ሄጄ ቁጭ እላለሁ፡” አለ። “ዛሬ ማታ እዚህ መድረክ ላይ እርሱን ለማጋለጥ ዝግጅት ላይ ናቸው፡” አለ። “እኔ በበርካታ ከባባድ ውጊያዎች ውስጥ አይቼዋለሁ፡ እግዚአብሔርም ሲታደገው አይቻለሁ፡” አለ። “ወደ ኋላ ሄ—ሄጄ ልቀመጥ፡” አለ።

141 ተነሳሁና ወጣሁ። እንዲህ አልኳቸው፡ “ዛሬ ማታ እዚህ መድረክ ላይ እንደምጋለጥ አንዲት ጽሁፍ እያነበብኩ ነበር።” “የኤፍቢአይ አባላት አሁን ወደ ፊት እንዲመጡ እና እዚህ በመድረኩ ላይ እንዲያጋልጡኝ እፈልጋለሁ፡” አልኳቸው። እንዲህ አልኳቸው፡ “እዚህ የምቆመው የወንጌልን ጠበቃ ለመሆን ነው፣ መጥታችሁ እንድታጋልጡኝ እጠይቃችኋለሁ” አልኳቸው። ጠበኳቸው። “ምናልባት ገና አልደረሱም ይሆናል፡” አልኩኝ። ሰራዬን አውቄው ነበርና። ከዚያ ከመውጣቴ በፊት፡ አስቀድሞ በክፍል ውስጥ፡ ምን እንደሚሆን አሳይቶኛል፡ አያችሁ። እኔም አልኩ፡ “ምናልባት ትንሽ እጠብቃለሁ። መዝሙር እንዘምር፡” ብዬ ጠየቅኳቸው? አንድ ሰው መጥቶ ሶሎ መዝሙር ዘመረ።

142 እኔም አልኩ፡ “ሚር. የኤፍ ቢ አይ አባል፡ ከውስጥ ነህ ወይስ ከውጭ? ለመጋለጥ እየጠበኩ ነው። እስኪ ወዲህ ትቀርባለህን? ” ማንም አልመጣም። የት ይሆን ብዬ ማሰብ ቀጠልኩ። እነ ማን እንደሆኑ ጌታ አስቀድሞ ነግሮኛል። ከእምነት ባክ ያደረጉ ሁለት ሰባኪዎች ናቸው፡ እ—እኔም እያየኋቸው ነበር። ጥቁር ጥላ ጥግ ላይ ተንጠልጥሎ አየሁ። የት እንደነበረ አወቅኩት። ወደዚያ ተመለከትኩ፡ እና ወደ ላይ ተንቀሳቀሰ እና ወደ ደረጃው እንደዚህ ወጣ። አንደኛው ሰማያዊ ልብስ የለበሰ፡ ሌላኛውም ግራጫ ልብስ የለበሰ ሰው ነበር።

143 እኔም “ወዳጆቼ፡ ኤፍቢአይ አይደሉም። ኤፍቢአይ መጽሐፍ ቅዱስን ከመሰበክ ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር አለው፡” አልኳቸው? እኔም፡ “በእርግጥ አይደለም። ሁለት የኤፍ ቢ አይ ወኪሎች እኔን ለማጋለጥ አልመጡም።

ነገር ግን፡ ይሄውና የምጋለጥ ነገር፡ እነዚያ ሁለት ሰባኪዎች፡ እዚያ እላይ ተቀምጠዋል።" እነርሱም ወረዱ። እኔም፡ "እንደዚያ አትውረዱ" አልኳቸው። ሁለት ትላልቅ ቴክሳኖች ወደዚያ ሄደው ልይዙዋቸው ነበር። እኔም፡ "አይ፡ ወንድሞች፡ ይህ የሥጋና የደም ጉዳይ አይደለም፡ ዝም ብላችሁ ተቀመጡ። እግዚአብሔር ይቆጣጠረዋል" አልኩ።

144 እኔም፡ "አሁን፡ ወንድሞች ሆይ፡ ተመልከቱ፡ እላይ እያላችሁ፡ ወደዚህ-ተመልከቱ" አልኳቸው። እንግዲህ አልኳቸው፡ "እኔን ጠ... ጠንቋዩ ስምዖን ነው ካላችሁ፡ በድግምት፡ ሕዝቡን እየጠነቁልኩባቸው ከሆነ።" እንዲህ አልኳቸው፡ "እኔ ጠንቋዩ ስምዖን ከሆንኩ፡ እናንተ የእግዚአብሔር ሰዎች ናችሁ ማለት ነው። እንግዲያውስ ኑና ወደዚህ ወደ መድረኩ ውጡ። እኔ ጠንቋዩ ስምዖን ከሆንኩ፡ እግዚአብሔር እኔን በሞት ይቅሰፈኝ። እኔ የእግዚአብሔር ነቢይ ከሆንኩ ግን፡ ኑ ውረዱና እግዚአብሔር እናንተን በሞት ይቅሰፋችሁ። አሁን ማን ትክክል እንደሆነ እና እንዳልሆነ እናያለን። አሁን ወደ ታች ኑ። እኛ መዝሙር እንዘምራለን" አልኳቸው። ከዚያም ከሕንጻው ወጡ፡ ከዚያ ወዲህ አላየናቸውም። አያችሁ? እንዲህ አልኳቸው፡ "እንግዲያውስ፡ እኔ ጠንቋዩ ስምዖን ከሆንኩ፡ እግዚአብሔር በሞት ይቅሰፈኝ። እኔም የእግዚአብሔር ነቢይ ከሆንኩ፡ ወደዚህ መድረክ ሰትመጡ እግዚአብሔር እናንተን ይቅሰፍ። እኔ በእግዚአብሔር ፊት እውነት ከሆንኩ፡ እግዚአብሔር በዚህ መድረክ ላይ እንድትሞቱ ያደርጋችኋል።" የሚሻላቸውን ያውቁታል። በትክክል። የሚሻላቸውን ያውቁታል። ከሌሎች ቦታዎች ሰምተው ነበርና። በትክክል። እግዚአብሔር አሁንም እግዚአብሔር እንደሆነ አስቡ እንጂ ሌላ ነገር አታሰቡ። እርሱ ይመልሳልና።

145 አሁን፡ ይህች ዓይን-ዶር ጠንቋይ፡ የሳሙኤልን መንፈስ ጠርታ አወጣች። ሳኦልም ከሳሙኤል ጋር ተነጋገረ። አሁን፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ዛሬ ሊሆን አይችልም። አይ፡ ወዳጄ። ምክንያቱም፡ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም የሙላት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ሞግዚት ነበርና። በእነዚያ ቀናት አንድ ሰው ሲሞት... ሰባኪዎች፡ ይህ ትክክል ነው ብላችሁ የሚታሰቡ ከሆነ እግዙኝ። አንድ ሰው ሲሞት፡ በእንሰሳ ቤዛነት አልፎ፡ ነፍሱ ወደ ገነት ትሄዳለች። በዚያም እስከዚያ ቀን ድረስ፡ እስከ መቤዠት ቀ—ቀን ድረስ ኖረ። ነፍሱም በዚያ ነበረች።

146 እዚህ ላይ ትንሽ ሰዕል ልሳልላችሁ። ጽሑፌን ያነበባችሁት ሰንቶች ናችሁ፡ ወይም ስለ ጥቅምትና፡ ህዳር ጉዳይ **በሪደርስ ዳይጀስት** ዕትም ላይ፡ ስለ እኔ የጻፉትን ጽሑፍ ያነበባችሁት ሰንቶች ናችሁ? መልካም። ያ እንዴት እንደነበረ አሰተውላችኋል? ከሁለት ወይም ከሦስት ሳምንታት በፊት፡ ይህች ታዋቂ መገናኛ ብዙኃን፡ ከረጅም ጊዜ በፊት፡ በወይዘሮ ፓይፐር ሙከራ ተደርጐባት እንደነበር፡ አሰተውላችኋል። **በሪደርስ ዳይጀስት** ላይ፡ የፓይፐር ጽሑፍ ያነበበ ሰው አለ? እነዚህ ሁለት መናፍስቶች አይገርሙም ወይ...

147 ምን ያህል ጊዜ ይቀረናል? ብዙም አይደለም ትንሽ ብቻ። ሃያ ደቅቃ ይቀረኛል፡ ፈጠን ፈጠን ማለት አለብኝ። ተመልከቱ፡ ለ... ለአንድ ደቂቃ ይቅርታ አድርጉሉኝ።

148 ውሸት እ—እንዳለ፡ ታውቃላችሁ። እውነትም ውሸትም አለ። አንድ

ዶላር ብሰጣችሁና፡ "ይህ ትክክለኛው ዶላር ነውን?" ብዬ ብጠይቃችሁ፡ ትፈትሹታላችሁ፡ በጣም ትክክለኛ ዶላር ካልመሰለ አትተማመኑበትም። ልክ ነው? ስለዚህ እጅግ በጣም ጥሩ መመሳሰል ሊኖረው ይገባል።

149 ኢየሱስም በመጨረሻው ዘመን ሁለቱ መናፍስቶች ቢቻል ኖሮስ የተመረጡትን፡ ሃይማኖታዊ ሰዎች እስኪያስቱ ድረስ በጣም ቅርብ ይሆናሉ ብሏል። አሁን አስታውሱ። አሁን፡ በውስጣቸው ምንም ነገር የለም-... ቀ-... ቀዝቃዛ፡ መደበኛ ናቸው። ከውጪ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ አያችሁ። ነገር ግን እነዚህ ሁለት መናፍስቶች፡ ዋናዎቹ መናፍስቶች፡ ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳ እስኪያታልሉ ድረስ በመጨረሻው ዘመን ጎን ለጎን ይሰራሉ። ኢየሱስ አላለምን? ብሏል።

150 አሁን ተመልከቱ፡ ወዳጆቼ፡ አንድ ትንሽ ሰዕል እስልላችኋለሁ። እዚህ ላይ አንድ ደቂቃ እንድትመልከቱ እፈልጋለው። ሙሉ ትኩረታችሁን ስጡኝ፡ ምክንያቱም አንድ ምሳሌ እሰጣችኋለሁ፡ ከዚያም ታዩታላችሁ።

151 አሁን፡ **በሪደርስ ዳይጀስት** ጋዜጣ ላይ፡ እዚያ ተጽፏል፡ እዚያ ቆሜ፡ እንዲጸለይላቸው የሚጠብቁ ሁለት ሺ ሰባት-መቶ ሰዎች፡ በዚያ ቆመው ነበር። ጋዜጣውን አንብባችኋል። ከካናዳ የመጣ አንድ ሰው ነበረ፡ ህጻን ልጁም በማዮስ እና በጆንስ ሆፕኪንስ ውስጥ ታይቶ ነበር፡ ትናንሽ እጆቹን ወደ ውስጥ **እንደዚህ** የሳበው ከባድ የአንጎል በሽታ ነበረበት፡ እግሮቹን ደግሞ ከታች ወደላይ የተሳበ ነበር። እነርሱም "ኦፕሬሽን ወይም ሌላ ምንም ማድረግ አይቻልም፡" አሉ።

152 ስለዚህ ወደ ካናዳ ይዞት ተመለሰ። እርሱም "አሁንም ተስፋ አልቆርጥም፡" አለ። በህዳር እትም **በሪደርስ ዳይጀስት** ጋዜጣ ታገኙታላችሁ፡ እና የ—የ—**የዶኒ ሞርተን ተአምር** ተብሎ ይጠራል። ከ—ከዚያም እንዲህ አለ፡ እዚያ፡ ሰ—ሰውየው እንዲህ አለ፡ "አሁንም ተስፋ አልቆርጥም፡ ምክንያቱም ዊልያም ብራንሃም የተባለ የእምነት ፈዋሽ አውቃለሁ፡ ይህም ሁለት ደንቆሮ እና ዲዳ የሆኑ ጓደኞቼ እንዲናገሩ እና እንዲሰሙ አድርጓቸዋል" አለ።

153 አሜሪካ ውስጥ፡ የ—የት እንዳለሁ ለማወቅ ሞክረው ደወለሉኝ። እኔም በኮስታ ሜሳ፡ ካልፎርኒያ ውስጥ ነበርኩ። ጽሑፍ ነው፡ በምታነቡበት ጊዜ፡ ልታለቅሱ ትደርሳላችሁ። ብቻ ልባችሁን ይሰብረዋል። ከህጻን ልጅ ጋር፡ እንዴት በበረዶ ክምር፡ እና በሁሉም ነገር ውስጥ እንደሄደ! እንዲህ አለ፡ "ዶኒ፡ ጠንቀቅ በል" አለው። "ይኸውልህ፡ አልተሸነፍንም፡" አለው። እናም ብላቴናው ፈገግ ማለት እንኳ አልቻለም፡ በጣም፡ ተጎድቶ ነበርና። እንዲህ አለው፡ "ገና አልተሸነፍንም፡ እግዚአብሔርን እንጠይቀዋለን። ወደ እግዚአብሔር ነቢይ እንሄዳለን እሱን እንጠይቀዋለን አለ።"

154 ከዚያም በበረዶው ውስጥ ተሻግረው መጡ። በመጨረሻም ወደዚያ ወረዱ፡ እናቱም አብራቸው እየመጣች ነበር፡ እናም በአውሮፕላን ለመሄድ በቂ ገንዘብ አልነበራቸውም፡ ስለዚህ እናቲቱን ወደ ኋላ እንድትመለስ አደረጉ። ልጁ እና አባቱ በአውቶቡስ መምጣት ነበረባቸው፡ እንዴት ከዊኒፔግ፡ ካናዳ፡ እስከ ኮስታ ሜሳ፡ ካሊፎርኒያ ድረስ ተጓዙ። ወደዚያም ደረሱ፡ ገንዘባቸውን ጨረሱ፡ አባቱም ልጁ ያደርገውን ዳይፐር ይቀይርለት እንደነበር፡ ብላቴናው

ሰባት ወይም ሰምንት ዓመት ገደማ ነው፡ በፍጹም የሚረዳው እንዳልነበረው ይናገራል። ለ... ለመብላትም ሆነ ለሌላ ነገር ዕድሉን አላገኘም፡ ብላቴናው እሱ ሲናገር መሰማት ብቻ እንደሚችል ተናግሯል። ታውቃላችሁ፡ ፈገግ ለማለት እየሞከረ መሆኑን፡ በዓይኖቹ በ—በሚያዩበት መንገድ ሊናገር ይችላል። በ... በአሜሪካ ውስጥ እያየ ያለውን የተለያዩ እይታዎችን፡ እንደሚነግረው ያውቃል።

155 ወደ ካሊፎርኒያ፡ ሲደርሱም፡ ለጉዞው ረዳት፡ ምን ለማየት እንደመጡ ነገሩት። እርሱም፡ “መለኮታዊ ምን ለማየት መጣችሁ? ” አለ በትልቅ የጥያቄ ምልክት።

156 እርግጥ ነው፡ አሜሪካ በጉዳዩ ላይ ምን እንዳለች መገመት ትችላላችሁ፡ አያችሁ። አያችሁ፡ እኛ ይህ ነን፡ አያችሁ፡ “ብልሆች ነን! ሁሉንም እናውቃለን፡ ታውቃላችሁ፡ ምንም ነገር ለእኛ መናገር አያስፈልግም። ሁሉንም ነገር ጽፈን ይዘናል።” አያችሁ?

157 ስለዚህ ከዚያም፡ ስለዚህ፡ “መለኰታዊ ምን? ከዊኒፔግ፡ ካናዳ ተጉዞ መጣ? ” ለምን፡ እነርሱ እጅግ መጃጃል ነው ብለው አሰቡ።

158 ያም ሆነ ይህ፡ ጋዜጠኞች መኪና አ—አዘጋጅተው ወደዚያ ላኩ። እናም፡ ወደዚያ፡ ወደ ጸሎት መሰመሩ ሲደርሱ፡ ሁለት-ሺ ሰባት መቶ ሰዎች እንዲፀለይላቸው እየጠበቁ እንደነበር ዘገቡ። ነገር ግን፡ የታመመው፡ ምስኪን-መሳይ ብላቴና፡ እና ያንን ምስኪን አባት የነተበ ኮፍያ አጥልቆ፡ የነተበ ኮት ለብሶ ሲያዩ፡ ሁሉም ሰው ወደ ጐን ገለል እንዲል እንዲል እና ቦታውን እንዲሰጡት አደረጉ። መድረኩ ላይ ሲወጣ...

159 የጸሎት ካርድ መለዋወጥ ደንቡን የሚፃረር ነው። ሰው ወደ ሰብሰባው መጥቶ የራሱን ካርድ ማግኘት አለበት። የጸሎት ካርዶችን ለሌላ ሰው ሲቀያይሩ፡ በመሰመር ላይ ቢገኙ፡ የጸሎት ካርዱ ክብር አልባ ነው። አያችሁ? ምክንያቱም መመሪያዎችን ለመስማት እና እንዴት መቀበል እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ። ይህ ሰለ እናንተ ነው። ሰለ ሌላ ሰው ካርድ መቀበል አይቻልም። እናንተ ራሳችሁ መጥታችሁ መውሰድ አለባችሁ፡ ስለዚህ ሰሙ። አንድ አንጋፋ ሰው እንዲህ አለ፡ “እ... እንግዲህ፡ እኔ በዚህ ነገር ላይ ብዙም አላምንበትም። ምናልባት ግን፡ እሱ ከፈወሰኝ፡ እ... ” አያችሁ? ይህም መሰውያው ላይ ጥሩ ያልሆነ ነገር አስከተለ፡ ስለዚህ ከመድረሱ በፊት ያንን ነገር ከለከሉት።

160 ስለዚህ ብላቴናው፡ ወይም አባቱ ወደ መሰውያው መውጣት ሲጀምሩ፡ ከሕዝቡ ቀድመው፡ መድረክ ሲወጡ ቢሊ የጸሎት ካርድ አለህ ብሎ ጠየቀው። ምንም አልነበረውም። “እንግዲያውስ አይቻልም፡ ወዳጄ፡” አለው። “መጠበቅ አለባችሁ፡” አላቸው።

161 እርሱም “እሺ፡” አለ። “እጠብቃለሁ፡” አለ። እንዲህ አለ፡ “እንግዲያውስ፡ እንደ ሌሎቹ ተራዬን እጠብቃለሁ።” “ይህን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር፡” አለ።

162 እና እኔ ከአንድ ሰው ጋር እየተነጋገርኩ፡ በመሃል ሰማኋቸው። ያ አባት ሲመለስ አየሁት፡ እናም እንዲህ አልኩት፡ “ችግሩ ምን ነበር? ”

እርሱም “የጸሎት ካርድ የለውም፡” አለኝ።

የሆነ ነገር “ና በለው፡” አለኝ።

163 ስለዚህም “ወደዚህ አምጣው፡” አልኩት። አባቱም መጣ፡ እና እምባው በፊቱ ላይ እየፈሰሰ ነበር፡ ጽሙም አድጎ ነበር። እ—እርሱም መድረኩ ላይ መጣ፡ **ሪደርስ ዳይጀስት** የዘገበው ይህ ነው። አያችሁ? ምንም ጥያቄ አልጠየኩትም፡ ነገር ግን በህጻኑ ፊት በማየት፡ ልጁ ከየት እንደነበረ ተናገርኩ፡ በማዮ ክሊኒክ እንደነበረ፡ ምን ችግር እንደነበረበት ሁሉ፡ እንዴት እንዳመመው፡ ሁሉንም ነገር ነገርኩት።

164 አባቱም ማልቀስ ጀመረ፡ እና መሄድ ጀመረ። መድረኩን ትቶ መሄድ ጀመረ፡ እና ቆም አለና ወደ ኋላው ዞሮ፡ “ትክክል ነው፡ ጌታዬ፡” አለ። እንዲህ አለ፡ “ልጄስ በህይወት ይኖራልን? ”

165 እኔም “ያንን ማለት አልችልም፡” አልኩት። “ትንሽ ጠብቀኝ፡” አልኩት። ያን ጊዜ ራዕይ ሲገለጥ አየሁ። እንዲህም አልኩት፡ “ይህንን ፈጽመህ አታምነውም፡ ምክንያቱም ማዮስ እና ሆፕኪንስ ሁለቱም በዚያ አንጎል ላይ ቀዶ ጥገና ሊደረግ እንደማይችል ተናግረዋል፡ እኔ ግን ምን ማድረግ እንዳለብህ እነግርሃለው። አንተ፡ ነገ፡ ከዚህ ሕፃን ጋር ሂድ። በሚቀጥሉት ሶስት ቀናት ውስጥ በመንገድ ላይ ጥቁር-ጸጉር ያላትን ሴት ታገኛለህ፡ ያችም ሴት የህጻኑ ችግር ምን እንደሆነ ትጠይቅሃለች። እና ከዚያም ቀዶ ጥገናውን ሊያደርግ ስለሚችል ስለ አንድ ትንሽ የገጠር ሐኪም ትነግርሃለች፡ አንተ ግን ማዮስ ውድቅ ስላደረገውና ‘ሊሆን የማይችል ነው፡’ ብሎ ስለተናገረ፡ ማመን አትፈልግም። ነገር ግን ይህ ልጅህ ያለው ብቸኛው እድል ያ ነው፡ በእግዚአብሔር ኃይል አማካኝነት፡ ያለው የእግዚአብሔር ምሕረት እና ይህ ቀዶ ጥገና ነው። አሁንም፡ እኔ የእርሱ ነብይ እንደሆንኩ የምታምን ከሆነ፡ የምነግርህን አድርግ አልኩት።” በሕዝቅያስ ላይ የበለስ ጥፍጥፍ እንደማስቀመጥ እና ወዘተ ማለት ነው።

እንዲህ አለ፡ ዞር ብሎ፡ “አመሰግናለሁ።” አለና ሄደ።

166 ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቀናት በኋላ፡ አንድ ቀን በጐዳና ላይ ነበር፡ እነሆም አንዲት እመቤት መጣች፡ እንዲህም አለችው፡ “የልጅህ ችግር ምንድነው? ”

167 እርሱም “የ—የአንጎል በሽታ ነው፡” አላት። እናም እንደዛ ንግግር ማድረጉን ቀጠለ። እና፡ መልካም፡ እ—እነርሱም እጅግ አስከፊ ነገር ነው አሉና፡ ታውቃላችሁ።

168 ስለዚህ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አንድ ነገር ሆነ አለ። እሷም “ወዳጄ፡ ይህን ቀዶ ህክምና ማድረግ የሚችል ሰው አውቃለሁ፡” አለችው።

169 እርሱም “እመቤቴ፡ ይኸውልሽ፡ የማዮ ብራዘርስ ተስፋ ቆርጠውበት ቀዶ ጥገና መደረግ እንደማይችል ተናግረዋል፡” አላት። እንዲህ አላት፡ “ወንድም ብራንሃም የሚባል አንድ ሰው ስለ እሱ እየጸለየ ነበር።” አላት፡ “ለህፃኑ ጸሎት አድርጓል።” እርሱም “እንዴ ቆይ እስኪ! ጥቁር-ጸጉር ያላት፡ ግራጫ ኮት ልብስ የለበሰች፡” ብሎ ነበር። “እሷ ነች፡” አለ። እርሱም፡ “ዶክተር የት ነው? ” እርሷም ነገረችው። ወደዚያ ወሰደው እና ሐኪሙ ቀዶ ጥገናውን አደረገለት፡ ህፃኑም ደህና ሆነ።

170 አሁን፡ ያ **በሪደርስ ዳይጀስት** በኩል መጣ፡ አያችሁ። እና ማዮ ብራዘርስ ለዚያ ቃለ መጠይቅ ጠሩኝ። “ሬቨረንድ ብራንሃም፡ ህፃኑን ምን አደረግክለት፡” ብለው ጠየቁኝ?

171 እኔም “ምንም። ፈጽሜ አልነካሁትም። እግዚአብሔር እንድነግር የነገረኝን ብቻ ነው የነገርኩት። ሰውዬውም ታዘዘ፡” አልኳቸው።

172 አሁን፡ በጣም የሚያሰቀው ነገር፡ ከዚያ ከሁለት ሳምንታት በኋላ፡ ወይም ከዚያ ከሁለት ሳምንታት በፊት፡ ወይም ሶስት ሳምንታት፡ **በሪደርስ ዳይጀስት** ላይ፡ ምናልባት ከአንድ ወር በፊት፡ የሚስ ፓይፐር ጽሁፍ ወጣ። አሁን፡ እሷ ትክክለኛ ጠንቋይ፡ ወይም ሙታን ሳቢ ነች። ይኸውላችሁ፡ ትክክለኛ አለ፡ አስመሳዮችም አሉ። ከ1897 ጀምሮ ያቺን ሴት ትታወቃለች። አሁን በኒው ዮርክ፡ ከመቶ ዓመት፡ በ... በላይ ሆኗታል። **የሪደርስ ዳይጀስት፡** ይ... መሰለኛል ከእኔ ሁለት ወር ወይም አንድ ወር ቀደም ብሎ ያወጣው ይመሰለኛል፥ በመኸር መጀመሪያ ላይ፡ ሊደርሳችሁ ይችላል። በቀደም ሚስተር ባክስተር አንድ ይዞ ነበር። አሰቀድሜ አሰቤው ብሆን ኖሮ፡ አመጣው ነበር... ወይም ይህን እንደምናገር አውቄ ብሆን ኖሮ፡ ይ—ባመጣሁት ነበር። ላመጣላችሁ እችላለሁ። ባለ አሥራ ሁለት ወይም አሥራ አራት ገጾች ናት። ሴቲቱ ተራ የቤት እመቤት የነበረች ነች። አንድ ቀን በሥቃይ ውስጥ ሳለች፡ ራሷን ሳተችና፡ ከሙታን ጋር መነጋገር ጀመረች። እና ያቺ ሴት በዓለም ዙሪያ፡ በሁሉም ቦታ ወሰዷት። ወደ እንግሊዝ ወሰዷት። ስህተቶችና ሌሎች ነገሮች መኖራቸውን ለማየት፡ ደጋግመው፡ ልብሷን ሳይቀር ቀይረዋል፡ በዚያም፡ አንድ ግሪካዊ ሰው ፊት ላይ ጭንብል አድርገው፡ እንደ እንግሊዛዊ ሰው አስመሰለው በፊቷ አመጡት። እሷም ሁሉንም ነገር ነገረችው። እሱም ከ—ከ—ከሞቱት ወዳጆቹ አንዱን መጥራት ፈለገ።

173 አሁን፡ የእሷ አንዱ ነገር... በመላው ዓለም ነው፡ እዚህ ላይ **የሪደርስ ዳይጀስት** የተናገረው ነው፡ እዚህ ከጥቂት ምሽቶች በፊት፡ ወይም ከጥቂት ወራት በፊት፡ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ተጋልጧል። አንዱ የእናንቱን የመንፈስ እጅ ሰሟል ተባለና፡ በሚቀጥለው ቀን በፖሊስ ፍርድ ቤት የተረጋገጠው የአይብ መጭመቂያ ጨርቅ እንደሳመ ነበር። የሙታን ሳቢነት ብዙ ሰዎች ያሰመሰሉታል! እነዚህ በየጎዳናው በመንገድ ዳር ላይ እየተቀመጡ የሚያነቡ ናቸው፡ ከጅምሩም ሙታን ሳቢዎች አይደሉም። እነዚህ የሐሰት አሰመሳዮች እንጂ ሌላ አይደሉም። ትክክለኞች ግን አሉ።

174 እኛም ሃይማኖተኞች ላይ፡ በሁለቱም በኩል ብዙ አሰመሳዮች አሉን። አሁን ለትንሽ ደቂቃ በእርጋታ አዳምጡኝ።

175 አሁን አስተውሉ፡ ሚስ ፓይፐር እውነተኛ ሙታን ሳቢ ነች። መጽሔቱ እንዲህ አለ፡ “በእርግጠኛነት መናገር የምንችለው አንድ ነገር አለ አሉ፡ ያም፡ አንድ ሰው ሲሞት፡ በእርግጥ አልሞተም ብለው ጽፈዋል። የሆነ ቦታ እየኖረ ነው፡ ምክንያቱም ያች ሴት መንፈሳቸውን ወደ ኋላ ትጠራለች እና ከሰዎች ጋር ትነጋገራለች።”

176 “አሁን፡ ወንድም ብራንሃም፡ ምን ታደርጋለች? ይህን ታምናለህ” ብትሉኝ? አዎን፡ ወዳጄ። መጽሐፍ ቅዱሰም ይመሰክራልና፡ ስለዚህም አምነዋለሁ። ከዲያብሎስ ናት። መናፍስታዊነት የዲያብሎስ ብልሃት ነው። አሁን ልብ በሉ፡ ሁለቱም ተመልከቷቸው።

177 እና የእሷን ተከትሎ የእኔ አንቀጽ በወጣ ጊዜ፡ ያን ጊዜ፡ ምን ያህል ደብዳቤዎች ወደ እኔ እንደጎረፉ ባያችሁ። ከዘመን ፍጻሜ በፊት፡ እግዚአብሔር

እነዚህን ነገሮች መናገሩ፡ እንግዳ ነገር አይደለምን? ***ሪድርስ ዳይጀስትም*** ከሰማይ በታች ባሉ ቋንቋዎች ሁሉ አትመውታል። አያችሁ? አስተውሉ፡ እርስ በርስ መከታተላቸው እንግዳ ነገር አይደለምን?

178 ደብዳቤዎች ይመጣሉ፡ እንዲህ ይላሉ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ይህ አንተም ሙታን ሳቢ መሆንህን ማረጋገጫ ነው።” አሉ፡ “ይህ ማረጋገጫ ነው። እስኪ ተመልከት፡ ስለ ሴቲቱ የት እንደምትገኝ ተናግረሃል... **ይቺን** ሴት ተመልከት? ”

179 እኔም “ቆይ አንዴ፡” አልኩ። ለሕዝቡ ለመላክ፡ (ይቅርታ)፡ ኦፊሺያል ደብዳቤ ይዣለሁ። እኔም “እናንተ ሰባኪዎች የምታውቁት ነገር በጣም ትንሽ ነው፡” አልኳቸው። “ሰውነታችሁን ከማጥመቅ ይልቅ አንጎላችሁን ማጥመቅ አለባችሁ፡” አልኳቸው። በትክክል። “ነገሮችን ለማሰብ ቆም አትሉም። ለመረዳት አትሞክሩም።”

180 በሌሎቹ ቀናት ያደርጉት የነበረው በተመሳሳይ መንገድ ነው። ኢየሱስንም አዩ። አቅሙን ተረድተውታል... የልባቸውን ምስጢር ያውቃል። እንደዚያ የሚያደርጉትን ለምን እንደሆነ ያውቃል። እነርሱም “የአጋንንት አለቃ ነው። እርሱ በዓለም ላይ ምርጥ ሟርተኛ፡ በዔልዘቡብ ነው፡” አሉት። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማየት፡ ለማወቅ ለመሞከር ቆም ማለት አልቻሉም። ይህን ለማወቅ በቂ መንፈሳዊ አልነበሩም። ያ ነው በቃ፡ ነገሮችን ያነባሉ። እርግጥ ነው፡ ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ፡ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት፡ ውዘተረፈ ይገባው ነበር፡ እነርሱ የሚመለከቱት ግን ዳግም ምጽአቱን ነው።

181 ዛሬም ያው ነው! ከእውነተኛ ነገር ባሻገር ሌላ እየተመለከቱ ነው። ሃሌሉያ! በትክክል። እግዚአብሔር ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ እዚህ እንዳለ አውቃለሁ፡ ብዙ ጊዜያችሁን እንደወሰድኩ አውቃለሁ፡ ነገር ግን ይህንን ማየት አለባችሁ፡ ጓደኞቼ። ዳግመኛ ካላየኋችሁ፡ አጋንንት ምን እንደሆኑ፡ እውነትና ስሕተት ምን እንደሆኑ ማወቅ አለባችሁ። በጣም የተቀራረበ ነው፡ ያንን ነገር መለየት አለባችሁ።

182 አሁን አስታውሱ፡ እዚያ ውጭ አይሆንም፡ **በዚህ** በኩል እንደ ፈሪሳውያን የሆነ ነገር አይሆንም፡ ወይም **በዚያ** በኩል የሆነ ነገር አይሆንም። እዚህ በር ላይ ነው፡ ከበር አጠገብ ነው። ተጠንቀቁ። አሁን...

183 እስቲ እነዚህ ሁለት ነገሮችን እንውሰድ። ዶላር ወስጄ ብሰጣችሁ፡ እንግዲህ፡ ሐሰተኛ ዶላር ብሰጣችሁ። ይህን መረዳት እንድትችሉ አንድ ምሳሌ እንጠቀማለን። ብልህ ሰው ከሆናችሁ፡ በቅድሚያ የምታደርጉት ነገር ቢኖር አንድ ዶላር አንሥተህ ብታየው፡ የመጀመሪያው ነገር፡ ከምን እንደተሰራ ዳሰሳችሁ ታያላችሁ። ልክ ነው? የተሰራበትን ነገር ትመለከታላችሁ። ዋጋውን ትመለከታላችሁ። እውነተኛ ዶላር ከወረቀት የተሰራ አይደለም፡ በከፊል ከወረቀት እና ከሃር የተሠራ ነው፡ አያችሁ። የመጀመሪያው ነገር፡ ዋጋውን መመልከት አለባችሁ። ያ የመጀመሪያው አመላካች ነው።

184 እናም አሁን እሷን **ከዚህ** ጐን እንውሰዳት፡ ጌታንም **በዚህ** ጐን እንውሰደው፡ እርሱም በእኛ ይሰራል።

185 አሁን ተመልከቱ፡ ማስተዋል ያለባችሁም የመጀመሪያው ነገር፡ ሁሉም ነገር... እንቀጹን እንብቡት። የሟቾችን-መናፍስት በመጥራት በቆየችባቸው፡ ኀምሳ-ዓመታት ውስጥ፡ አንድም ቀን ስለ እግዚአብሔር፡ ስለ ክርስቶስ፡

ስለ መለኮታዊ ፈውስ፡ ስለ መዳን፡ ስለ ፍርድ፡ ወይም ስለ ሌላ ነገር አልተናገረችም። በዚህ ውስጥ ከጨዋታና ከሞኝነት በቀር ምንም ነገር የለም።

186 **በዚህ** በኩል ግን፡ ዘወትር እግዚአብሔር፡ ፍርድ፡ የኢየሱስ መምጣት፡ መለኮታዊ ፈውስ፡ መለኮታዊ ኃይል፡ ነጻ መውጣት አለ። ዋጋውን ተመልከቱት። ጠንቋዮችና አስማተኞች ወንጌልን ሲሰብኩ አይታዩም። የሕዝቡ ችግር ምንድነው? ማይ! ልብ በሉ!

187 ማድረግ ያለባችሁ እውነተኛው ነገር፡ እውነተኛ ዶላር መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ በጣም የሚመስል ከሆነ፡ ቁጥሮቹን ጽፋችሁ ወደ ማምረቻው ላኩላቸው። ከዛ ጋር የሚዛመዱ ቍጥሮች ካሉ፡ እንግዲያውስ የብር ዶላር ይጠብቃችኋል። ልክ ነው?

188 መልካም፡ ስለዚህ፡ ወንድሜ፡ የሴቲቱ ሰራም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መልሰው፡ የዓይን-ዶር ሟርተኛ እንደሆነች ትረዳለህ።

189 ይኸኛውም ውስዱትና፡ ታገኙታላችሁ፡ እዚህ በዋናው ማምረቻ ውስጥ ባለው መፅሃፍ ላይ ነው፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" በእርግጠኛነት፡ የእርሱ ተመሳሳይ ሥራ! እርሱ ሰዎች ጋር በሞኝነት እና በእርባናቢስነት አልተመላለሰም። አንድን ሰው ለመርዳት፡ ወደ እግዚአብሔር፡ ለመምራት ነው እንጂ። አሜን! እኔ ራሴ ስለ ራሴ "አሜን" እያልኩ አይደለም፡ ነገር ግን **አሜን** ማለት "እንዲሁ ይሁን" ማለት ነው። አ... አምናለው። እውነት እንደሆነ አውቃለሁ።

190 ይኸውላችሁ፡ አሁን አስተውሉ። አሁን፡ ፈጠን ብለን፡ ምክንያቱም ብዙ ላቆያችሁ ስለማልፈልግ ነው።

191 እዚህ፡ እዚህ ላይ ትንሽ ስዕል እንውሰድ፡ ትንሽ የአዕምሮአዊ ስዕል። በዚህ በኩል አንድ ጅረት አለ፡ **በዚህ** በኩል ወደ ታች ይወርዳል፡ በሕይወት በኩል ይወርዳል። አሁን ተመልከቱ። ይህ ሰርጥ ነው። አሁን ያልተከፋፈለ ትኩረታችሁን ስጡኝ፡ ስለዚህ ይህ እንዳያመልጣችሁ። ልክ **እንደዚህ** ወደ ታች ይወርዳል። አሁን፡ በዚህ ትንሽ ሰርጥ ውስጥ እኔና እናንተ፡ ሟች ፍጥረታት እንኖራለን። አሁን፡ እዚያ ውስጥ፡ ምን እንዳለ እንመልከት። የጅምላ ሞኝነት እና ሌሎች ነገሮች ናቸው፡ አንዳንዴ ግን ብርሃን ታያላችሁ። መጨለምና ጎዳናዎችን ታያላችሁ፡ ግብረ ሰዶማዊነትና ሸክም-ነው፡ ዲያብሎስ ሰዎችን ይይዛል። ኦህ፡ ጥሩ ይለብሳሉ፡ ማይ፡ በተቻለ መጠን ከፍተኛ ባህል አላቸው፡ ስኮላሮች አሏቸው፡ ነገር ግን አሁንም ዲያብሎስ ነው። ዳግም-የተወለደው ግን በዚህ መልኩ ተቀምጧል።

192 አሁን፡ በዚህ ቻናል ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል። አሁን፡ በዚህ በኩል **በዚህ** መንገድ-ሲሄዱ፡ ሥላሴ አለ። በዚህ በኩል **በዚህ** መንገድ-ሲሄዱም፡ ሥላሴ አለ።

193 አሁን፡ አሁን፡ የመጀመሪያው ቦታ፡ **በዚህ** ጐን፡ **የዓመፀኞች** ነፍሳት ናቸው፡ አንድ ሰው ሲሞት ፍርድ ወደሚጠባበቅበት ሰፍራ ይሄዳል። ኢየሱስም ሄዶ በዚያ ለታሰሩት ነፍሳት ሰበከ። በቀጣዩ አጋንንት ናቸው። ቀጣዩ ደግሞ፡ በሲኦል ውስጥ ያለው ዲያብሎስ ነው። ወደ ላይ ስንሄድ፡ የመጀመሪያው፡ አሁን፡ እነርሱ ውስጥ በዚያ መናፍስት ናቸው፡ ፈጽሞ ንስሐ ያልገቡ የሞቱ የሰዎች መናፍስት

አሉ። የፍርዱንም ቀን ይጠባበቃሉ። የሚያውቁት ብቸኛው ነገር ሞኝነት እና ያደረጉት ነገር ነው።

194 አሁን፡ እዚህ ላይ፡ እነዚህ ክርስቲያኖች ከላይ ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል። ይህ ምሳሌ ነው። እዚህ ላይ ሌላ መንፈስ አለ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የሰው መንፈስ፡ እርሱም ክርስቶስ ኢየሱስ። መንፈስ ቅዱስ፡ መንፈስ ቅዱስ በዚህ በሟች ዓለም ውስጥ በቤተክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

195 ዲያብሎስ፡ **በእነዚህ** መናፍስት አማካኝነት፡ በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ቀጣዩ መላዕክት ናቸው። ቀጣዩ እግዚአብሔር ነው። አሁን፡ እዚህ ያለው እያንዳንዱ ሟች ከእነዚህ ዓለማት በአንዱ ተጽዕኖ ይደረግበታል። ምን ለማለት እንደፈለኩ አያችሁ?

196 አሁን ያቺ ሴት ያደረገችው፡ ወደዚያ አድማስ ሰብራ ገብታለች። በመጀመርያም፡ ንስሃ ያልገቡትን፡ እነዚያን በአጋንንት-የተያዙ የወደቁት መላእክቶች መናፍስት የሆኑትን ሰውነታቸውን እንዲይዙ የፈቀዱትን፡ አጋንንት ያደረባቸውን ሰዎች እየተናገረች ነው። የፍርዱንም ቀን ይጠባበቃሉ።

197 **እነዚህ** ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ተጽዕኖ የተደረገባቸው እና ዳግመኛ የተወለዱ ናቸው። ዲያብሎስ የራሱ ነቢያት አሉት፡ እግዚአብሔርም የእርሱ ነቢያት አሉት። ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህ ተጽዕኖ ነው፡ እና እንቀጥል። መለየት እንድትችሉ ቆም በሉ። ኢየሱስ፡ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ...

198 አሁን፡ ዛሬ፡ ወደዚያ ዓለም ዘልቆ በመግባት ጻድቅ የሆነን ሰው ከዚያ ዓለም ማስወጣት አይቻልም። ይህን ማድረግ አይቻልም፡ ምክንያቱም ጻድቃን ሰዎች ቀደም ሲል በነበሩበት ሙታን ማቆያ ሰማይ ውስጥ፡ አይደሉም። አይደሉም፡ ወዳጄ። የኢየሱስ ደም ካጠበው በኋላ፡ የሙታን ማቆያ ሰማይ አብቅቶለታል። ወደዚህ እዩ። ማይ!

199 ኢየሱስ ሲሞት፡ በወኅኒ ላሉት ነፍሳት እንዴት እንደሰበከ፡ ማሰብ ከቻልን እንዲህ ነው። እርሱ ኃጢአትን ሳያውቅ፡ ኃጢአተኛ ሆኖ፡ ሞተ፡ ሆኖም ኃጢአታችን በእርሱ ላይ ነበር። እግዚአብሔርም፡ ስለ ኃጢአቱ፡ ወደ ሲኦል ላከው። መጽሐፍ ቅዱስም "እርሱም ሄዶ ለነፍሳት ሰበከ፡" ይላል።

200 አንዳንድ ሰዎች "ወንድም ብራንሃም፡ ልረዳው አልቻልኩም፡" ይላሉ። እንዲህ ይላሉ፡ "ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ተነሣ። አርብ ከሰዓት በኋላ ሞቶ እሁድ ጠዋት ተነስቷል፡ ለምን፡ እርሱ የሞተው አንድ ቀን ብቻ ነው።"

201 "በጊዜው፡" ብሎ መለሰ፡ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጥቅስ ስለነበረው፡ የጸናባት አንዲት ቃል ነበረችው። ዳዊት፡ በኋላ ከእምነት ባክ ያደረገ፡ ነገር ግን የዳነ፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት፡ ነቢይ የሆነ ሰው ነውና፡ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡ "ነፍሱን በሲኦል ውስጥ አልተወውም፡ ቅዱሱንም መበስበስን እንዲያይ አልሰጠውም።" በሦስት ቀንና ሌሊት፡ ሥጋው እንደሚበሰብስ፡ አወቀ። እግዚአብሔርም ለነቢዩ እንዲህ አለው፡ "መበስበስን አያይም።"... ? ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

ሃሌ ሉያ! የእግዚአብሔርን ቃል አመነ። በእርሱ ላይ፡ ሁል ጊዜ፡ ሰይጣንን ድል አደረገ። በእግዚአብሔር ቃል፡ ሞትን አሸነፈ። ሃሌ ሉያ! ሞትን አሸንፏል።

በገደሉትም ጊዜ፡ ኃጢአተኛ ሆኖ፡ ሞተ፡ ኃጢአቴና ኃጢአታችሁ በእርሱ ላይ ሆነ፡ ወደ ጥልቅ ወረደ፡ በዚያ በር ሲያንኳኳ ይታየኛል።

እነዚያም የጠፉ ነፍሳት ወጥተው እንዲህ አሉ፡ “ታዲያስ፡ አንተስ ማን ነህ? ”

202 እርሱም እንዲህ አለ፡ “ሄኖክን ለምን አልሰማችሁም? እነዚያን የሰበኩትን ሌሎች ነቢያት ለምን አልሰማችሁም? ” የተፈረደባቸው ናቸው። “እኔ በአንድ ወቅት ህያው የሆንኩ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። እነሆ... ደሜ ፈሰሷል። ልነግራችሁ የመጣሁት፡ ማድረግ ያለብኝን ነብያት የተናገሩትን ነገር፡ እኔ ፈጽሜዋለው።” በቀጥታ ወዲያው-አጋንንትን አልፎ፡ ወደ ሲኦል ደረሰ፡ የሞትና የሲኦል ቁልፎችን ከዲያብሎስ ወሰደ፡ በጎኑም አንጠለጠላቸው፡ ወደ ኋላም መመለስ ጀመረ። ሃሌሉያ!

203 በማለዳ ለመነሳት። ሃሌሉያ! እዚህ ላይ አንድ ትንሽ ሰዕል እንሳል። በጠዋቱ፡ ሌላ ቡድን እዚህ በሙታን ማቆያ ሰማይ ተኝተው ነበር። አሁን በዚያ የሉም።

204 አሁን፡ በቅዱሳን አማላጅነት የምታምኑ ትልልቅ የካቶሊክ ወዳጆች። በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ ከአንድ ጻድቃን ጋር እየተነጋገርክ ከሆነ፡ ያ ሰው ኃጢአተኛ ነው፡ እሱ ሲኦል ውስጥ ነው፡ ወይም—ወይም ፍርዱን እየጠበቀ ነው። ጻድቃን ከሆነ፡ በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ ነውና ወዲህ አይመለስም። በትክክል። ያን ማረጋገጥ እችላለሁ። የኮርማዎች ደም ኃጢአትን አያስወግድም፡ የኢየሱስ ደም ግን ከኃጢአት ጋር ያፋታል።

205 ኢየሱስ ወደ ገነት ሲሄድ፡ ይታየኛል፡ የጥንቱ አብርሃም፡ ይስሐቅ እና ያዕቆብ፡ ሌሎቹም በዚያ ውስጥ፡ ሳሙኤል እና የተቀሩት ሁሉ በዚያ ውስጥ ነበሩ። በሩን ሲያንኳኳ ይሰማኛል። [ወንድም ብራንሃም መድረኩን አንኳኳ—አርታዒ።] አሜን! ኦህ፡ ይህንን ባረከኝ። እ... አሁን እምነት እምነት አለኝ። ወደ ማዶ ሲመለከት እየዋለሁ። “ማን ነህ? የሚያንኳኳው ማን ነው? ” ሲል ይሰማኛል፡ እርሱም “እኔ ነኝ፡ ይህ የሚናገረው አብርሃም ነው። ማን ነህ? ”

206 “እኔ የአብርሃም ዘር ነኝ።” አሜን። አብርሃም ወደ በሩ ሲመጣ፡ በሩን ሲከፍተው እያለሁ። እርሱም “እኔ የአብርሃም ዘር ነኝ፡” አለ።

ዳንኤልም “ተመልከቱ! ከተራራው ሲወጣ ያየሁት ድንጋይ ይህ ነው፡” አለ።

207 ሕዝቅኤልም እንዲህ ሲል እሰማዋለሁ፡ “እርሱ ነው! ደመናዎች ከእግሩ በታች፡ እንደ ትቢያ-ሲንቀሳቀሱ፡ አይቼው ነበር፡ አውራ በጎች... እጆቻቸውን አጨበጨቡ፡ ቅጠሎቹም፡ አጨበጨቡ እና ሁሉም ጮኹ። ኦህ፡ በሙታን ማቆያ ሰማይ ውስጥ እሱን የሚጠብቁትን የተለያዩ ሰዎችን፡ እያለሁ።

208 አንደኛው እንዲህ ሲል ይሰማኛል፡ “ኑ! በኢየሩሳሌም የፀሐይ ብርሃን በርቷል። ከዚህ መውጣት አለብን። ወደ ላይ እናርጋለን፡ ደሜን እየጠበቃችሁ፡ በኮርማዎች እና በፍየሎች ደም ታምናችሁ ጠብቃችኋልና። አሁን ግን ደሜ በቀራንዮ ላይ ፈሰሷል። እኔ በሰጋ የተገለጥሁ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። የኃጢአት ዕዳዎች ሁሉ ተከፍለዋል። ለመውጣት መንገድ ላይ ነን!” ሃሌሉያ! ክብር ለእግዚአብሔር!

209 አብርሃም ሣራን በክንዱ ሲይዛት ይታየኛል፡ ሲወጡም፡ በማቴዎስ 27 ላይ፡ እሱ በወጣ ጊዜ! ወዲያው ወጡ፡ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ትንሽ ቆም ሲሉ ይሰማኛል። እና በመጀመሪያ የሆነው ነገር፡ ቀያፋ እና ሌሎች ሰዎች በጐዳና ላይ ቆመው፡ እንዲህ ሲሉ እያለሁ፡ "ሰውዬው ተነስቷል እየተባለ ነው። ንገሩኝ፡ ያ ወደዚያ የሚሄደው ሰውዬ ማን ነው፥ ያ ወጣት፡ ያች ወጣትስ እነማናቸው? "

210 ከእንግዲህ ወዲህ አላረጁምና፡ አብርሃምና ሳራ ናቸው። በቅጽበት ጥፍት አሉ። ተመለከቱ፡ "አንድ ሰው እየተመለከተን ነው።" እሱ በግድግዳው ውስጥ እንዳለፈ፡ ሊሰወሩ ይችላሉ አካላቸው አንድ አይነት ነው። ሃሌ ሉያ! በትክክል። እነሆ ሁሉም ነቢያትና ሌሎቹ፡ ከተማይቱን እየዞሩ፡ እየተመለከቱ ነበሩ።

211 ኢየሱስም ከዋክብትን፡ ጨረቃንና፡ ደመናዎችን፡ አልፎ ወደ ላይ አወጣቸው፡ ምርኮንም ማረከ፡ ለወንዶችም ስጦታ ሰጠ። ኢየሱስ ዛሬ በአብ ቀኝ ተቀምጧል፡ ወደ ላይ ወጣ፡ ተቀመጠ፡ ጠላቶቹ ሁሉ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ።

212 ዛሬም፡ ውድ ክርስቲያን ወዳጄ፡ አጋንንት በእያንዳንዱ እጅ ላይ እየሰሩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በየጊዜው፡ ይቃወመዋል። ሃሌ ሉያ! እነሆ እናንተ። ጋዜጦች እና ሪደርስ ዳይጀስቶች ሁሉም ነገሮች እያወጁ ነው። እየተመለከቱት ነው። ምን እንደሆነ ማየት አይችሉም። ይህ ምንድን ነው? ይህ በእግዚአብሔር እና በዲያብሎስ መካከል በቅርቡ የሚመጣው፡ የታላቁ ትዕይንት ጥላው ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ወግንና በልብህም ውስጥ ትክክል ሁን። አሜን።

213 እዚህ ባለፈው ጊዜ በቶሌዶ፡ ኦሃዮ፡ ውስጥ ስብሰባ ላይ ነበርኩ። አሁን እዘጋለሁ።

214 ስለ አጋንንት ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ? እየሰሩ ነው። ልክ እንደ ሃይማኖተኛ፡ በጣም ሃይማኖተኛ ናቸው! ኦህ፡ በየሳምንቱ እሁድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፡ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ ይደግማሉ፡ እንዲሁም ዶክሶሎጂ ይዘምራሉ። ኦህ፡ ማይ፡ በቃ የቻሉትን ያህል ሃይማኖተኛ!

"ወንድም ብራንሃም፡ እውነቱ ይህ ነው ማለትህ ነው? "

215 ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ የሰቀለው እንዲህ ዓይነት መንፈስ ነው። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡ "እናንተ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ።"

216 አሁን አንዳንዶች "ኦ ሩሲያ ጸረ ክርስቶስ ናት፡" ይላሉ። በጭራሽ! ሩሲያ ጸረ ክርስቶስ አይደለችም። ጸረ ክርስቶስ በጣም ሃይማኖተኛና ቢቻለውስ የተመረጡትን እንኳ የሚያስት ነው።

አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ሰውየውን ይወስዳል እንጂ፡ መንፈሱን ፈጽሞ አይወስድም። ዲያብሎስም ሰውየውን ይወስዳል እንጂ፡ መንፈሱን አይወስድም። አሁን፡ ተመልከቷቸው። ራሳችሁን ፈትሹ። እኔ ለእውነት ብቻ ተጠያቂ ነኝ።

217 አጋንንቶች፡ በስራ ላይ ናቸው! ትናንት፡ በሥጋዊ አድማስ አይተናቸዋል። ዛሬም፡ በመንፈሳዊው አድማስ ውስጥ፡ በሃይማኖታዊው አድማስ ውስጥ መኖርያቸው። እዚያ ያሉበት፡ ካንሰር ይሉታል፡ ሌሎቹም **ይህን፡ ያንን፡ ሌላውን** ብለው ይጠሩታል፡ እኔ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት፡ አጋንንት

መሆናቸውን፡ አረጋግጫለሁ። አሁን፡ እዚህ፡ ዛሬ፡ አሁንም በሃይማኖት አድማስ፡ በጣም ሃይማኖተኛ፡ በጣም አክራሪ ናቸው።

218 ማሰብ፡ ከጀመርክ፡ ወንድሜ። ቃየን፡ በመጀመሪያ ላይ፡ በጣም ሃይማኖተኛ ሰው ነበር። ኤሳው በጣም ሃይማኖተኛ ሰው ነበር። ይሁዳ በጣም ሃይማኖተኛ ሰው ነበር። ሃይማኖት ነው። ውጫዊው ዓለም አይደለም። በደረጃዎች ውስጥ ነው። አጋንንቶችን፡ ተጠንቀቁ! ምናልባት ትንሽ በኋላ ላይ፡ የሆነ ጊዜ፡ ትንሽ ተጨማሪ መነጋገር እችላለው። ብዙ እየቆየን ነው።

219 ማንንም አትኮንኑ። ሁሉንም ውደዱ። ከልባችሁ መውደድ ካልቻላችሁ፡ ክርስቶስ ከእናንተ ጋር አይደለም።

220 በቶሌዶ፡ ኦሃዮ፡ ትንሽ ምግብ ቤት ገባሁ። በአንድ ቦታ፡ ትንሽ ዱንከርድ ይሆን ቦታ፡ ቆንጆ ትንሽ ቦታ እየበላሁ ነበር። በጣም ጥሩ ነበሩ። የዚያን ቀን ከሰአት በኋላ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ስለሄዱ፡ ዝግ ነበር። እነሱ ሲዘጉ፡ መንገዱን አቋርጬ፡ ወደ ዓለማዊ ትንሽ ቤት መሄድ ነበረብኝና፡ እዚያ ገባሁ። በኦሃዮም ውስጥ ቁማር መጫወት ህገወጥ እንደሆነ አውቃለሁ። እና የግዛቱ ፖሊስ ሴት አቅፎ ቆሟል፡ እጁ በጡቶቿ ላይ ተንጠልጥሎ፡ የቁማር ማሽን እየተጫወተ ነው። የክልላችን እና የሀገራችን ህግ ሁሉ፡ ጠፍቷል። ያሳዝናል!

221 በጠንካራው ዓለት በክርስቶስ ታምኛለሁ፡ ቆሜያለሁ፡ ሌሎች ቦታዎች ሁሉ የሚያሰምጡ አሸዋዎች ናቸው። ሌላ ምንም አልቀረም። በትክክል።

222 ዞር ብዬ አማትሬ አየሁ፡ አንዲት ቆንጆ ወጣት ነበረች፡ ምናልባት በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ፡ አሥራ ዘጠኝ፡ አሥራ ሰምንት፡ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ይሆናታል። ሲሰሩት የነበረው ነገር፡ በጠረጴዛው ዙሪያ የነበሩ ልጆች የሚያደርጉት ነገር፡ አሰቃቂ ነበር። እኔ ቁጭ አልኩ። አሁንም የደነቀኝ ሁኔታ፡ እዚህ ቁጭ ብዬ ሳለሁ፡ አንድ እመቤት መጥታ፡ "ወንበር ትፈልጋለህ" አለችኝ?

እኔም "አመሰግናለሁ። ቁርስ ፈልጌ ነበር፡" አልኳት።

223 ወንበር ላይ ተቀምጬ፡ አንዲት አሮጊት እመቤት ተቀምጣለች፡ እንደ እናቴ ዕድሜ፡ ኀምሳ-አምስት፡ ኀምሳ-ሰምንት ዓመት ይሆናታ። እነዚያ የሚለብሷቸውን እግዚአብሔርን የምጻረሩ መጥፎ ልብሶች ለብሳ ነበር።

224 ጥሩ ነው ይላሉ። በፍጹም፡ ጥሩ አይደለም። ሳይንስ "አብዳችኋል፡" ብሏቸዋል። እርቃናችሁን ማሳየት ብቻ ነው የፈለጋችሁት። አሳፋሪ፡ ውርዴት ነው። እመቤት እነዚያን አትለብሰም። ሴት ልትለብሰው ትችላለች፡ እመቤት ግን አትለብሳቸውም።

225 እና ከዚያ፡ እ—እዚያ፡ ተቀምጣ ነበር። ሥጋዋ ተሸብሽቧል። የኦርኪድ-መልክ ጥፍር ቀለም ተቀብታለች፡ ምን ብላችሁ ነበር የምትጠሩት፡ እርሱንም ከንፈሯ ላይ ቀብታ ነበር። እንዲሁም እንደ ወንድ፡ ሙሉ በሙሉ ፍሪዝ የተሰራ አጭር ጸጉር፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፡ ይህም ውርዴት ነው ይለዋል። አንዲት ሴት፡ አንድ ወንድ...

226 መጽሐፍ ቅዱስ፡ አንዲት ሴት ፀጉሯን ብትቆርጥ፡ ወንድ በፍቺ ሊፈታት መብት እንዳለው ይወሰናል፡ ምክንያቱም ለእሱ ታማኝ አይደለችም። በእነዚህ ቀናት ውስጥ ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስን መሰበክ አለብን። "ፀጉሯን ብታሳጥር፡ ባሏን ታዋርዳለች፡" ይላል። ክብሯን የማትጠብቅ ከሆነች፡ መፈታት

አለባት። አንተም ሌላ ማግባት አትችልም፡ እሷን መተው ግን ትችላለህ። ዋው! ቦይ፡ ይህ፡ ይህ እየከበደ እንዳለ፡ ይሰማኛል። እውነታው ግን ይህ ነው።

227 ኦህ፡ በመንፈስ ቅዱስ አድማስ ውስጥ፡ ይህ ነገር ይዘን ነበር፡ ግን አጥሩን ጥሰናል። አንድ ሽማግሌ ወንድማችን እንዲህ ይል ነበር፡ "አጥሩን ጥሰናል፡ አጥሩን ጥሰናል፡ በኃጢአት ላይ አመቻምቸናል። አጥሩን ጥሰናል፡ በጎቹ ወጥተዋል፡ ፍየሎች ግን እንዴት ገቡ?" አጥሩን ጥሳችኋል። ያ ነው ችግሩ። አጥሩን ጥሳችኋል፡ ዓለምን እና ቤተክርቲያንን ቀላቅላችኋል። እንደ ሞዓባውያን እና ሌሎች፡ እና በለዓም፡ መካከላቸው እንዴት እንደተጋባ፡ ዛሬም በትክክል ተመሳሳይ ነገር ነው። ቤተ ክርስቲያንም በሙላት ተበክላለች፡ እና ለብ ያለውም፡ የጴንጤቆስጤው ዘመን የሎዶቅያ ዘመን ነው፡ ከእግዚአብሔርም አፍ ተተፍታለች። ከእያንዳንዳቸው ወገኖችም፡ እግዚአብሔር የራሱ ቅሬታዎች ጠራ፡ በትንሣኤ አማካኝነት፡ ወደ ቤቱ ይወሰዳታል፡ ያ በትክክል እውነት ነው፡ በትክክል።

228 በዚያም ተቀምጣ፡ ፊቷ ላይ ሁሉ የከንፈር ቀለም ሞልቶ፡ ሁሉም እንደዛ ሆና ነበረች። እዚህም ላይ ጥቁር ነገር በአይኗ አከባቢ ነበር፡ ያልባትም ነበር፡ እየፈሰሰ ነበር። ምናልባት ምስኪኗ አሮጊት የልጅ-ልጆች ይኖሯት ይሆናል። እሷም በሁለት ሽማግሌዎች ተቀምጣ ነበር፡ እና ከእነርሱ አንዱ አንገቱ ዙሪያ ትልቅ ሻርፕ ጠምጥሞ ነበር፡ በሰኔ ወር ውስጥ፡ በዚያ ተቀምጠው ነበር። እርሱም ተነሣ፡ ይጠጣ ነበር፡ እሷም፡ ትጠጣ ነበር። እና ዙሪያዋን ትመለከት ነበር።

229 እኔም እንዲህ አሰብኩ፡ "አምላክ ሆይ! አምላክ ሆይ፡ ይህን ነገር ከምድር ገጽ ለምን አታጠፋውም? ለምን? ትንሿ ሻሮኔ… ትንሿ ልጄ፡ ትንሿ ሣራዬ እና ትንሿ ርብቃዬ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ለመጋፈጥ፡ በዚህ ትውልድ ውስጥ ማደግ አለባቸውን?" እንዲህ አሰብኩ፡ "በእነዚህ ፓርኮች እና ነገሮች ውስጥ፡ ምን እየተከናወነ እንዳለ ተመልከት።" እንዲህ አሰብኩ፡ "አምላክ ሆይ! ኦህ፡ ፈቃድህ ከነበረ ሳሮንን ስለወሰድክ ደስተኛ ነኝ። ትንሿ ሣራዬ እና የ—ትንሿ ርብቃዬ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ማደግ አለባቸውን?" ይህም፡ እነዚያ ሰዎች እራሳቸውን በኳየር… የሚዘምሩ እና ሁሉም ነገር ብለው ይጠራሉ። "ይህ ነውር አይደለምን፡" አልኩኝ? እኔም፡ "ጌታ ሆይ፡ ቅድስናህ እንዴት ታገሰው? የጽድቅህ ቊጣ በዚያ በመብረር ይህን ቦታ የሚያፈነዳው ይመስላል" ብዬ አሰብኩ።

230 የእግዚአብሔርም መልአክ፡ "ወዲህ ና፡" ሲለኝ ሰማሁት። ወደዚያም ተራመድኩ። ከእኔ ጋር ነገሩን በፈጸመ ጊዜ፡ እንደ ሌላ ሰው ሆንኩኝ። "ለምን ትኮንናታለህ?"

እኔም፡ "እስኪ ነገረ ስራዋ ሁሉ፡ ተመልከታት።" ይኸው የሱ ነገርም…

231 ራእይ አየሁ። **እንደዚህ** ያለ ዓለም፡ ክብ፡ ሌላ ዓለም አየሁ። ነገር ግን **ይህች** ዓለም፡ በዙሪያዋ ቀሰተ ደመና ነበራት፡ ይህም የእግዚአብሔርን ቊጣ የሚከላከል የክርስቶስ ደም ነበር። ይህ ማለት አያያትም፡ ቢ—ቢያያትማ እንደተናገረ፡ አሁኑኑ ያጠፋታል፡ "ከእርሱ በበላህ ቀን፡ በዚያ ቀን ትሞታለህ።" ስለዚህ ያደርገው ነበር።

232 ከዚያም እኔ እንደዚህ አሰብኩ። እኔ ራሴን አየሁ። ምንም እንኳ ያንን ባላደርግም፡ ለማንኛውም፡ ነገር ግን ኃጢአተኛ ነበርኩ። ከዚያም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለእኛ እንደ መከላከያ ሆኖ ያገለግላል። አያችሁ? ኃጢአት በምሠራ ጊዜ፡ ኃጢአቴ እርሱን ሲመታ ውድ ጭንቅላቱን ሲቀጠቅጥ፡ እርሱም እንባዎቹን እና ደሙ ሲፈስ አየሁ። “አባት ሆይ፡ የሚያደርገውን አያውቅምና፡ ይቅር በለው።” እኔም ሌላ ነገር አደርግና በሌላ ደግሜ እመታዋለው። “አባት ሆይ፡ ይቅር በለው።”

233 ይህ ሁሉ ከእሱ ቢያልፍ ኖሮ፡ ጠፍቼ ነበር። ጸጋውን በጭራሽ ካልተቀበልኩ፡ እና ነፍሴ ከዚያ ባሻገር በምትጓዝበት ቀን፡ ቀድሞውኑ ተፈርዶብኛል። ተወግዤያለው። ከፍርድ በቀር ምንም የቀረኝ ነገር የለም። ተፈርዶብኛል፡ ቀድሞውንም ተፈርዶብኛል። እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡ “ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ።” በትክክል ተፈርዶባችኋል። ይህ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ፍርድ ወንበር፡ በኢየሱስ ላይ ባላችሁ እሳቤ ላይ ነው።

234 ከዚያም “አዎ፡ ያ ትክክል ነው፡” ብዬ አሰብኩ። እኔም አንድ ቀን ወደ እርሱ አየሁ። ጥንታዊው መጽሐፍ በዚያ ተከፍቶ አየሁ፡ ኃጢአተኛ፡ በዚያም ሁሉ በዝርዝር ተቀምጦ ነበር። እነሆ ያን ሁሉ ያደረገ የራሴ ኃጢአት እንደሆነ ተገነዘብኩ፡ እንዲህ አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ ይቅር ትለኛለህን?

235 እጁን በጐኑ አሰገባና፡ የተወሰነ ደሙን አውጥቶ፡ በላዩ ላይ፡ “ይቅር ተብለሃል፡” ብሎ ጻፈ። በድጋሚ ላይታሰብ፡ ወደ መርሳት ባሕር ውስጥ ጣለው። ለዘላለም ጠፋ! እርሱ እንዲህ አለ “እኔ ይቅር አልኩህ፡ አንተ ግን እሷን ኮነንካት፡” አለኝ።

ይህ ሃሳቤን ቀየረው። “ጌታ ሆይ፡ ምሕረት አድርግልኝ፡” አልኩት።

236 ከዚያ ውስጥ ከወጣሁ በኋላ፡ ወደ እሷ ሄድኩና ተቀመጥኩ። እንዲህ አልኳት፡ “እንዴት ነሽ፡ እመቤት? ”

እርሷም “ኦህ፡ ሰላም፡” አለችኝ።

237 እኔም “ይቅርታ አድርጊልኝ” አልኳት፡ እኔም፡ “ሬቨረንድ ብራንሃም ነኝ፡ አገልጋይ ነኝ፡” አልኳት።

እሷም “ኦህ፡ ይቅርታ አድርግልኝ፡ ይቅርታ፡ ሬቨረንድ ብራንሃም፡” አለች።

238 እኔም፡ “እመቤት፡” ነገሩን ብቻ አጫወትኳት፡ እንዲህ አልኳት፡ “እዚያ ቆሜ ነበር፡ ምናልባት ልጆች ይኖሩሻል፡ እና እየኮነንኩሽ ነበር፡ በሃሳቤም “እንዴት ያለ አስቃቂ ነገር ነው! እያልኩ ነበር።”

እሷም “እሉኝ፡” አለች።

239 እኔም፡ “ነገሩ እንዲህ እንዲሆንብሽ ያደረገው ምንድን ነው? ” እሷም የሁሉንም ሰው ልብ የሚነካ ታሪክ ልትነግረኝ ጀመረች። እንዲህ አልኳት፡ “እግዚአብሄርን እንዲህ ያ—ያሉትን ሰዎች ከምድር ላይ ለምን አላጠፋቸውም ብዬ ስጠይቀው ነበር። እዚህ፡ እዚህ ከእነዚህ ሁለት ሰካራሞች ጋር ነሽ፡ አንቺ ራስሽ፡ ለራስሽ ጠጥተሻል።” እኔም፡ “አንድ ቀን... ያ ደም የእግዚአብሔርን ቊጣ ከአንቺ ያርቃል። ከእነዚህ ቀናቶች ውስጥ በአንዱ ትሞችያለሽ። ስለዚህ፡ አሁን፡ ነጻ የፈቃድ ምርጫ አ—አለሽ፡ መቃወም ወይም መቀበል ትችያለሽ አልኳት።” “አንድ ቀን ግን ነፍስሽ ከአድማስ ባሻገር ትሄዳለች፡ ምንም ምህረት

ወደሌለበት። በኃጢአትሽ ብትሞቺ፡ ቀድሞውኑ ተፈርዶብሻል፡ ወደ ገሃነምም ትሄጂያለሽ።”

240 ታውቃላችሁ? ያቺ ሴት በዚያ ምግብ ቤት ውስጥ ካለው ወንበር ላይ ተንሸራተተች። አናንተ በሕይወታችሁ ውስጥ ሰምታችሁ የማታውቁት አይነት የጸሎት ጉባኤ አደረግን፡ ወደ ክርስቶስም መጣች። ምን ነበር? አትፍረዱባቸው፡ ወንጌልን ንገሯቸው። በአጋንንት ተይዘዋል፡ በዚህ ዓለም ውስጥ ሟቾች ናቸው። ከዚህ በሚነሣ ተጽዕኖ ስር ናቸው። የእኛ ተጽዕኖ የሚመጣው ከላይ ነው። ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማሸነፍ በተሰጥኦዎቻችን፡ ምን ማድረግ እንደምንችል እንመልከት።

241 የሰማዩ አባታችን፡ ስለ ቸርነትህና ምሕረትህ አመሰግንሃለሁ። ይቅርታ፡ ጌታ ሆይ፣ ምናልባት፡ ህዝብህን፡ እዚህ ለረጅም ጊዜ ያዝኳቸው። ነገር ግን በእነዚህ ከሰዓት በኋላ ሰብሰባዎች መደምደሚያ እንደመሆኑ መጠን፡ “ስለ አጋንንቶች፡” ለመናገር ፈልጌ ነበር፡ እና በአንድ ሰብከት ውስጥ በአንድ ቦታ ላይ፡ በጣም ብዙ ቆራርጨዋለው፡ ምናልባት ግን ከዚህ እና ከዚያ፡ መረዳት ይችሉ ዘንድ፡ እና ምን ማለቴ እንደሆነ ይረዱ ዘንድ ነው። ይህን ለማምጣት፡ የልቤን ፍላጐት ታውቃለህ።

242 ሰዎች ዛሬ ከሰዓት በኋላ ከዚህ ሲሄዱ፡ ወንዶች እና ሴቶች የሚያደርጉትን እያንዳንዱን እንቅስቃሴያቸውን ይመልከቱ፡ ግን ደስተኛ እና ነጻ ሆነው ይኑሩ። እግዚአብሔር እንዳዳናቸው ሁሉም ይወቁ። ወደ እርሱ ተመልክተውም፡ በዙሪያቸው ያሉትን ሁሉንም ኢዝሞች እና ነገሮች ይርሱ፡ በሰላም እና በመጠን፡ እግዚአብሔርንም በመፍራት ይኑሩ። ከዚያም፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ በማንኛውም ነገር እነሱን ለመጠቀም ስትፈልግ፡ በቀጥታ ለእነሱ ማነጋገር እና ወደፈለግከው መላክ እንድያደርጉ የምትፈልገውን ነገር እንድያደርጉልህ ማድረግ ትችላለህ። ሰዎች ትሑታን ይሁኑ እና ክርስቶስን በልባቸው ያኑሩ። ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዳችን፡ በደላችንን፡ ይቅር በለን።

243 ሰይጣንም የ—የሚውጠውን እየፈለገ፡ በሁሉም ቦታ፡ እንደሚዞር አንበሳ፡ የሐይማኖት ካባ ለብሷል። እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህ ምስኪን ትናንሽ ልጆችን፡ በየቦታው፡ ተመልከታቸው። ለሕዝብ ክፍትና የተጋለጡ ናቸውና። አምላክ ሆይ፡ እኔ እጸልያለው፡ ምሕረት አድርግላቸው፡ የጠፉትን ሁሉ አድናቸው፡ የታመሙትን ፈውስ። እናም፡ አምላክ ሆይ፡ እነዚህ ያረጁ የበሽታ አጋንንቶች በልጆችህ ላይ እንደሚመጡ እናውቃለን፡ ይህን የሚያሰወግድ፡ የኃጢአትን ሰርየት በዚያ አለህ። ኃጢአት እንዲሠሩ በሚያደርጓቸው ሰይጣኖች ሁሉ፡ ይህን የሚያሰወግድ፡ የኃጢአት ሰርየት በዚያ አለህ። በኢየሱስ ስም እንድትሰጠን እጸልያለሁ። አሜን።

ምናልባት እኔ…

53-0609A አጋንንት፡ በሐይማኖታዊው አድማስ
ሮበርትስ ፓርክ አምፊቲያትር
ኮነርስቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org